# የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ
# የ2004 የባጀት/የትምህት ዘመን የስራ ክንውን ሪፖርት

ሐምሌ 2004
ዓዲግራት

## ይዘት


| ተ.ቁ. | ይዘት | ገፅ |
|---|---|---|
| 1 | መሰረታዊ አሃዛዊ መረጃ | 2 |
| | 1.1. ተማሪዎችና ትምህርት ክፍሎች | 2 |
| | 1.2. መምህራን | 6 |
| | 1.3. ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች | 8 |
| | 1.4. የ2004 መደበኛ ባጀት አጠቃቀም | 10 |
| 2 | የአመቱ እቅድ አፈፃፀም | 13 |
| 3 | የ2004 ባጀት/ትምህርት ዘመን አፈፃፀም ሰንጠረዥ | 28 |
| 4 | ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮችና የተወሰዱ/ሊወሰዱ የታቀዱ መፍትሂዎች | 38 |

## 1. መሰረታዊ አሃዛዊ መረጃ

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ በ2004 የትምህርት ዘመን ትምህርት የሚጀምሩ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ስራ በመጀመራቸው ምክንያት በሀገሪቱ ውስጥ ያሉት መንግስታዊ ዩኒቨርሲቲዎች ቁጥር 31 ደርሷል። ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ግንቦት 18/2003 በወጣው ነጋሪት ጋዜጣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 223/2003 "ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ" ተጠሪነቱ ለትምህርት ሚኒስቴር ሆኖ የተቋቋመ መንግስታዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው። እንደሌሎች የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ሶስት ዋና ዋና ተልእኮዎች ያሉት ሲሆን እነሱም፤ ተማሪዎችን በተለያዩ የትምህርት መስኮች ተቀብሎ ማስተማር፤ የምርምር ተግባራት ማከናወን፤ እና የህብረተሰብ አገልግሎት ስራዎችን መስራት ናቸው። ዩኒቨርሲቲው ከሰኔ አጋማሽ ጀምሮ በጊዚያዊነት በተከራየው ህንፃ እስከ ታህሳስ ግማሽ አከባቢ የቆየ ሲሆን ወደዩኒቨርሲቲው ግቢ ሙሉ ለሙሉ ተዛውሮ ስራውን በመስራት ላይ ይገኛል። ዘንድሮ ስራቸውን ከጀመሩት አዳዲስ ዩኒቨርሲዎች ውስጥ ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ በራሱ ግቢ /ሌሎቹ ዩኒቨርሲቲዎች ከግቢያቸው ውጪ ነው ስራቸውን የጀመሩት/ የተመደቡለትን ተማሪዎች ህዳር 24 እና 25 እንዲገቡ በማድረግ እና ህዳር 26 ደማቅ የአቀባበል ስነስርአት በማዘጋጀት ስራውን በይፋ ለመጀመር ችሏል። ኦርየንቴሽን፤ እና የትምህርት ክፍል መረጣና ምደባ ከተደረገ በኋላ ትምህርት ታህሳስ 9/2004 የጀመረ ሲሆን የአንደኛ ሰሚስተር ስራ ተጠናቆ የሁለተኛው ሰሚስተር ስራ ነሐሴ 2004 መጀመርያ ላይ ለማጠናቀቅ ዝግጅቶች በመደረግ ላይ ናቸው።

ዩኒቨርሲቲው አጠቃላይ ተግባሮቹን በሶስት ምእራፎች ማለትም፤ የመጀመርያው ምእራፍ የምስረታና የመቋቋም ምእራፍ፡ ሁለተኛው ምእራፍ የመጠናከርና የመደላደል ምእራፍ፡ እና ሶስተኛው ምእራፍ ደግሞ ብቁና ተወዳዳሪ ሆኖ የሚወጣበት ምእራፍ እንደሚኖረው ታሳቢ በማድረግ ስራዎቹን የጀመረ ሲሆን በተጀመረው የትምህርት ዘመን የዩኒቨርሲቲው ዋና ትኩረት የምስረታና የመቋቋም ምእራፍ ስራዎችን ትኩረት በመስጠት /ተገቢ አመራር የመፍጠር፤ አሰራሮችንና አደረጃጀቶችን የመንደፍና የማዘጋጀት፤ ዩኒቨርሲቲውን ለማቋቋም እና የመጀመርያ አመት ስራዎችን ለመስራት የሚያስችለው የሰው ሃይል እና የማቴርያል ፍላጎቶችን የማሟላት/ ለማከናወን ዝርዝር እቅድ አዘጋጅቶ በሰራተኞች ውይይት ተደርጎበት እና በቦርድ ፀድቆ የአመቱ ስራዎች ተጠናቋል። በዚሁም መሰረት የአመቱ የአፈፃፀም ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 1.1. ተማሪዎችና ትምህርት ክፍሎች

ዩኒቨርሲቲው የተቀበላቸው ተማሪዎች በትምህርት ሚኒስቴር የተመደቡለት ሲሆን የተመደቡት ተማሪዎች በአራት ባንዶች የተከፋፈሉ ናቸው። በአመታዊ ዝርዝር አቅዱ የምንቀበላቸው ተማሪዎች የግንባታው ሂደት መሰረት በማድረግ አንድ ሺ /የግንባታው የመጀመርያው ዙር ሩብ ክፋይ ብቻ የሚጠናቀቅ ከሆነ/ ወይም ሶስት ሺ /የግንባታው የመጀመርያው ዙር በሙሉ የሚጠናቀቅ ከሆነ/ ሊሆን እንደሚችል መቀመጡ ይታወሳል። አመታዊ ዝርዝር ፕላኑ ከተዘጋጀ በኋላ ባሉት ጥቂት ወራት ውስጥ መረዳት የተቻለው ሶስት አራተኛው ክፋይ በታሰበው ጊዜ ሊያልቅ እንደማይችል በመታወቁ ምክንያት መቀበል የምንችላቸውን ተማሪዎች እንድንገልፅ በትምህርት ሚኒስቴር በተጠየቅነው መሰረት 1040 ተማሪዎችን መቀበል እንደምንችል አሳውቀናል። ይሄንን መሰረት በማድረግ ትምህርት ሚኒስቴር የመደበልን የተማሪዎች ቁጥር 960 መሆኑንና የተመደቡት ተማሪዎችም ዝርዝር ልኮልናል። የተመደቡት ተማሪዎች በአራት ባንዶች ሲሆኑ /ኢንጂነሪንት፤ ተፈጥሮ ሳይንስ፤

ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፤ እና ሌሎች ማህበራዊ ሳይንስ/ በሚከተለው ሰንጠረዥ የተመለከተውን ይመስላል፤

ሰንጠረዥ 1. የተመደቡ ተማሪዎች በባንድ፤ በፆታና፤ በመጡበት ክልል

| Studets Placed at Adigrat UNIVERSITY | Engineering | Natural Sciences | Businesss and Economics | Social Sciences and Humanities | Total | % |
|---|---|---|---|---|---|---|
| Students by Gender | | | | | | |
| Male | 170 | 48 | 90 | 31 | 339 | 35.31 |
| Female | 234 | 215 | 102 | 70 | 621 | 64.69 |
| Total | 404 | 263 | 192 | 101 | 960 | 100.00 |
| Students by Region | | | | | | 0.00 |
| Addis Ababa | 37 | 15 | 34 | 1 | 87 | 9.06 |
| Afar | 3 | 2 | | 1 | 6 | 0.63 |
| Amhara | 28 | 21 | 9 | 9 | 67 | 6.98 |
| Benshangul Gumuz | 6 | 5 | | 1 | 12 | 1.25 |
| Diredawa | 3 | 2 | | | 5 | 0.52 |
| Gambella | | 1 | | | 1 | 0.10 |
| Harari | 2 | | 1 | | 3 | 0.31 |
| Oromia | 26 | 38 | 27 | 9 | 100 | 10.42 |
| Other Countries | 1 | | | | 1 | 0.10 |
| SNNP | 9 | 20 | 25 | 5 | 59 | 6.15 |
| Somali | 2 | 3 | | | 5 | 0.52 |
| Tigray | 287 | 156 | 96 | 75 | 614 | 63.96 |
| Total | 404 | 263 | 192 | 101 | 960 | 100.00 |
| % by Band | 0.42 | 0.27 | 0.20 | 0.11 | | |

በሰንጠረዡ እንደተመለከተው ከተመደቡት ተማሪዎች 65 ከመቶ የሚሆኑት /ማለትም 621 ተማሪዎች/ ሴቶች ናቸው። የሴቶች ቁጥር ከወንዶች ቁጥር የበለጠ መሆኑ የመኝታ ቤት፤ የሚቀጠሩት የመኝታ ቤት ተቆጣጣሪዎች ብዛት፤ የአካዳሚክ እና አስተዳደር ድጋፍ አሰጣጥ፤ የምክር አገልግሎት፤ እና ሌሎች ተጓዳኝ ነገሮች ይሄንን ስብጥር ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ መሰራት እንዳለበት የሚያመላክት ስለሆነ በዚሁ መሰረት ተሰርቷል።

የባንድ ስብጥር በተመለከተ ደግሞ የጠቅላላ ተማሪዎች 42 ከመቶ /ማለትም 404 ተማሪዎች/ በኢንጂነሪንግ ትምህርት መስኮች /ማለትም ባንድ አንድ/ ነው የተመደቡት። የተማሪዎችን ብዛት በተፈጥሮ እና በማህበራዎ ሳይንስ ሲታይ 69.5 ከመቶ በተፈጥሮ ሳይንስ መስክ የተመደቡ ሲሆን የተቀሩት 30.5 ከመቶ በማህበራዊ ሳይንስ መስክ የተመደቡ ናቸው። ስለዚህ አመዳደቡ አገሪቱ የምትከተለውን የ70 -  30 ስብጥር ከወዲሁ ያሟላ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

ተማሪዎች የመጡበት ክልሎችን በሚመለከት ደግሞ የተመደቡት ተማሪዎች ከሁሉም ክልሎች የተውጣጡ ሲሆን አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የመጡባቸው ክልሎች ደግሞ ትግራይ /64 ከመቶ/፤ ኦሮምያ /10 ከመቶ/፤ አዲስ አበባ /9 ከመቶ/፤ አማራ /7 ከመቶ/፤ እና ደቡብ ህዝቦች /6 ከመቶ/ ናቸው።

የተመደቡልን ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ያገኙት ውጤት በተመለከተ ሲታይ ደግሞ በሚከተለው ሰንጠረዥ የተጠቃለለውን ይመስላል፤

ሰንጠረዥ 2. የተመደቡ ተማሪዎች ባገኙት የመግቢያ ነጥብ

| ውጤት | ኢንጂነሪንግ | ተፈጥሮ ሳይንስ | ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | ማህበራዊ ሳይንስ | ድምር | ፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ≥400 | 6 | 3 | 1 | 1 | 11 | 1.1 |
| [350, 400) | 25 | 15 | 11 | 8 | 59 | 6.1 |
| [300, 350) | 145 | 45 | 79 | 28 | 297 | 30.9 |
| < 300 | 228 | 200 | 102 | 64 | 594 | 61.9 |
| ድምር | 404 | 263 | 192 | 101 | 960 | 100 |
| በአዎንታዊ ድጋፍ የተመደቡ | 88 | 146 | 23 | 29 | 286 | 29.8 |

በሰንጠረዡ እንደተመለከተው ወደ ዩኒቨርሲቲያችን ከተመደቡት ተማሪዎች ውስጥ በጣም አብዛኛዎቹ ያገኙት ነጥብ አነስተኛ እንደሆነ ለማየት ይቻላል። ከጠቅላላ ተማሪዎች ስልሳ ሁለት ከመቶ የሚሆኑት ያገኙት ወጤት ከ300 በታች ነው። የአመዳደቡ ስብጥር በተመለከተም ያለንን ቅሬታ የካቲት 2004 መቐለ ላይ በተካሄደው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የስድስት ወራት የአፈፃፀም ግምገማ ላይ አቅርበናል። በሌላ በኩል ደግሞ የተማሪዎቹ ውጤት ቀደም ብለን ያወቅነው ስለሆነ ከኮሌጆችና ትምህርት ክፍሎች ሃላፊዎችና ከመላው መምህራን ጋር ባደረግናቸው ውይይቶች የአብዛኛዎቹ የመግቢያ ውጤት አነስተኛ ቢሆንም ተማሪዎችን ለማብቃት በሚያስችለን መልኩ የተለያዩ ጥረቶችን ማድረግ እንደሚጠበቅብን መግባት ላይ ደርሰንበት በዚሁም መሰረት የሚመለከታቸው ኮሌጆች እና ትምህርት ክፍሎች የስራ መርሃ ግብር በማውጣት እና ከአንደኛ ሰሚስተር ውጤት መታወቅ በኋላ ደግሞ የማጠናከርያ ትምህርት /Remedial/ ስራዎች ተሰርተዋል።

ከላይ የተቀመጠው ማብራርያ በትምህርት ሚኒስቴር የተመደቡልን ተማሪዎችን የሚመለከት ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች /ማለትም የተመደቡት ተማሪዎች በሙሉ ሪፖርት ያላደረጉ በመሆናቸው፤ ከተመደቡት ውስጥ በዝውውር ወደሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች የሄዱ ስላሉ፤ እና ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችም ወደኛ በዝውውር የመጡ በመኖራቸው/ ትምህርት የጀመሩ ተማሪዎች ብዛት 898 ነው። በተለያዩ ምክንያቶች ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ዝውውር ወደ ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ከጠየቁት 27 ተማሪዎች ውሰጥ 22 የሚሆኑትን ተቀብለናቸዋል። የዝውውር ጥያቄው የታየው የረጂስትራር፤ የተማሪዎች ዲን፤ እና የትምህርት ክፍል ሃላፊዎች ያለው አንድ ኮሜቴ ተቋቁሞ ውሳኔ እንዲሰጥበት በማድረግ ነበር።

የተመደቡት ተማሪዎች ለህዳር 24 እና 25 ወደ ዩኒቨርሲቲው ሪፖርት እንዲያደርጉ በቴሌቪዥን ማስታወቅያ በተነገረው መሰረት ተማሪዎቹ በተጠቀሱት ሁለት ቀናት ውስጥ ወደ ዩኒቨርሲቲው ገብተዋል። **ማክሰኞ ህዳር 26/2004** ደግሞ የከተማው ነዋሪ ተወካዮች፤ ጥሪ

የተደረገላቸው እንግዶች ፤ እና የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እንዲሁም ተማሪዎች /በድምሩ ወደ 2000 ህዝብ/ በተገኘበት ደማቅ የእንኳን ደህና መጣችሁ ፕሮግራም ቀኑን ሙሉ ተዘጋጅቶ ዩኒቨርሲቲው **በይፋ ስራውን እንዲጀምር ተደርጓል።**

የተማሪዎች አቀባበል ከተደረገ በኋላ ህዳር 29/2004 በኮሌጅ ደረጃ ለተማሪዎች ኦርየንቴሽን የተሰጣቸው ሲሆን ኦርየንቴሽኑን ተከትሎ ከምህንድስና ውጭ ያሉት ተማሪዎች የትምህርት ክፍል ምርጫ አካሂደዋል። የምህንድስና ኮሌጅ ተማሪዎች ትምህርት ክፍል ምርጫ ያላካሄዱበት ምክንያት በመጀመርያው ሰሚስተር አንድ ላይ ሆነው የቅድመ ምህንድስና /Pre-engineering/ ኮርሶችን መውሰድ ስለሚኖርባቸው ነው። አንደኛውን ሰሚስተር ካጠናቀቁ በኋላ ደግሞ የትምህርተ ክፍል ምርጫ አካሂደው በቅድመ ምህንድስና የነበሩት ተማሪዎች ትመህርት ክፍሎቻቸውን እንዲያውቁ ተደርጎ የሁለተኛ ሰሚስተር ትምህርተ በየትምህርት ክፍሎቻቸው እንዲከታተሉ ተደርጓል።

የትምህርት ክፍል ምርጫን ተከትሎ መደረግ የነበረበት ተማሪዎችን በየትምህርት ክፍሉ በመመደብ ትምህርት መጀመር ሲሆን ምደባው የተማሪዎች ምርጫን መሰረት ያደረገ መሆን እንዳለበት በአመታዊ እቅዱ በተቀመጠው መሰረት ምርጫቸው እንዲታይ ተደርጓል። በዚሁም መሰረት በጊዜው የመረጡት ተማሪዎች ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ ድረስ ያስቀመጡት ምርጫ የሚከተለውን ይመስላል፤

ሰንጠረዥ 3. የትምህርት ክፍል ምርጫ

| ምርጫ | ተፈጥሮ ሳይንስ | | | | ማህበራዊ ሳንይስ | | ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፊዚክስ | ኬሚስትሪ | ባዮሎጂ | ሒሳብ | እንግሊዝኛ | ሲቪክስ | ማኔጅመንት | አካውንቲንግ | ኢኮኖሚክስ |
| 1ኛ | 3 | 57 | 164 | 5 | 2 | 86 | 66 | 68 | 38 |
| 2ኛ | 18 | 140 | 53 | 20 | 86 | 2 | 55 | 57 | 59 |
| 3ኛ | 99 | 18 | 6 | 104 | | | 47 | 45 | 16 |

በሰንጠረዡ እንደሚታየው ፊዚክስ፤ ሂሳብና እንግሊዝኛ በአንደኛ ምርጫ የመረጣቸው ተማሪ በጣም ትንሽ ነው። የተማሪዎችን ምደባ የሚሰራ አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ ምደባውን በማድረግ ሁሉም ትምህርት ክፍል ሃላፊዎች በተገኙበት መድረክ እንዲያቀርብ ከተደረገ በኋላ ሰፊ ውይይት ተደርጎበት እንዲሻሻል ተደርጓል። በዚሁም መሰረት ተማሪዎች እስከተቻለ ድረስ በመጀመርያ ምርጫቸው ቀጥሎም ሁለተኛ ምርጫቸው መሰረት በማድረግ እንዲመደቡ መደረግ እንዳለበት ስምምነት ላይ በመደረሱ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ያሉት ተማሪዎች በመጀመርያ ምርጫቸው መሰረት ሙሉ በሙሉ እንዲመደቡ ተደርጓል። ወደ ፊዚክስ፤ ሂሳብና እንግሊዝኛ ደግሞ በተቻለ መጠን በሁለተኛው ምርጫቸው እንዲመደቡ ተደርጓል። በዚህ የማይስማሙ ተማሪዎች ካሉ ደግሞ በማመልከቻ ጥያቄያቸውን እንዲያቀርቡ እድል እንዲሰጣቸው እና አንድ በአንድ እንዲታይ ተደርጓል። በዚሁም መሰረት የምደባው ዝርዝር ከወጣ በኋላ 23 የሚሆኑ ተማሪዎች ወደ ሌላ መቀየር እንደሚፈልጉ በማመልከቻ ጠይቀዋል። ካመለከቱት ውስጥ ሴት አመልካቾች ተለይተው /ከሁለቱ በስተቀር ሁሉም ሴት አመልካቾች ነው የነበሩት/ በፍላጎታቸው መሰረት እንዲመደቡ ተደርጓል። ከዚሁም በተጨማሪ የእርስ በርስ ዝውውር የጠየቁት በሙሉ ተፈቅዶላቸዋል። በዚሁም መሰረት የትምህርት ክፍል ምደባው የተማሪዎችን ፍላጎት መሰረት ባደረገ በጥሩ ሁኔታ ተሰርቷል። ዘግይተው የመጡት ተማሪዎች ደግሞ ባሉት ክፍት ቦታዎች ላይ እንዲመርጡ ተደርጎ ተመድበዋል።

ምደባው በዚህ መልኩ ከተሰራ በኋላ በያንዳንዱ ትምህርት ክፍል ትምህርት የጀመሩት የተማሪዎች ብዛት የሚከተለውን ይመስላል።

ሰንጠረዥ 4. በትምህርት ላይ ያሉ ተማሪዎች

| ት/ክፍል | የተማሪዎች ብዛት | | | ድርሻ /%/ | 70-30 ድርሻ /%/ | የሴክሽኖች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| ቅድመ ምህንድስና* | 173 | 207 | 380 | 42.32 | | 8 |
| ፊዚክስ | 6 | 31 | 37 | 4.12 | | 1 |
| ኬሚስትሪ | 9 | 69 | 78 | 8.69 | | 2 |
| ባዮሎጂ | 16 | 70 | 86 | 9.58 | | 2 |
| ሂሳብ | 12 | 35 | 47 | 5.23 | **69.93** | 1 |
| ማኔጅመንት | 29 | 35 | 64 | 7.13 | | 2 |
| አካውንቲንግና ፋይናንስ | 25 | 43 | 68 | 7.57 | | 2 |
| ኢኮኖሚክስ | 27 | 16 | 43 | 4.79 | | 1 |
| ስነዜጋና ስነምግባር | 22 | 33 | 55 | 6.12 | | 1 |
| እንግሊዝኛ | 10 | 30 | 40 | 4.45 | **30.07** | 1 |
| ድምር | 329 | 569 | 898 | 100.00 | 100.00 | 21 |
| ድርሻ /%/ | 36.64 | 63.36 | 100 | | | |

*የቅድመ ምህንድስና ተማሪዎች የትምህርት ክፍል መረጣ ያካሄዱት በሁለተኛ ሰሚስተር ሲሆን መረጣውም የተማሪዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ነው የነበረው። በዚሁም መሰረት በሲቪል ምህንድስና ሶስት ሴክሽኖች /በድምሩ 172 ተማሪዎች ከዚህም ውስጥ 106 ሴቶች/ ተመድበው በሌሎች ትምህርት ክፍሎች (ኤሌክትሪካል 56 ተማሪዎች -28 ሴት-፤ ሜካኒካል 56 ተማሪዎች -17 ሴት- ፤ ኬሚካል57 ተማሪዎች -28 ሴት- ) ደግሞ አንዳንድ ሴክሽኖች ተመድበዋል።በድምሩ 341 የኢንጂነሪንግ ተማሪዎች በሁለተኛው ሰሚስተር የተመዘገቡ ሲሆን በአንደኛ ሰሚስተር ከነበሩት 380 ተማሪዎች ውስጥ 39 ያህሉ በተለያየ ምክንያት ያቋረጡ ናቸው።*

ከላይ በሰንጠረገፑ እንደተቀመጠው በአንደኛ ሰሚስተር ትምህርት የጀመሩት ተማሪዎች ብዛት 898 ሲሆን ለሰሚስተሩ መጨረሻ ፈተና የተቀመጡት ተማሪዎች ብዛት ደግሞ 844 ነበር። ይህም ማለት 54 ተማሪዎች /6%/ በተለያየ ምክንያት ትምህርት ያቋረጡ ናቸው። ትምህርት ካቋረጡት ውስጥ 16 ተማሪዎች /ሴቶች 11/ ዊዝድረዋል ሞልተውና ምክንያታቸው ተቀባይነት አግኝቶ ያቋረጡ /Withdrawals/ ሆነው የተቀሩት 38 /ሴቶች 28/ ደግሞ በራሳቸው ምክንያት ዊዝድረዋል ሳይሞሉ ያቋረጡ /Dropouts/ ናቸው። ለመጨረሻ ፈተና ከተቀመጡት ውስጥ 25 ተማሪዎች /0.3%/ በአካዳሚያዊ ጉድለት ምክንያት የተባረሩ ሆነዋል።

## 1.2. መምህራን

በአመታዊው ዝርዝር እቅድ እንደተመለከተው ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ 174 መምህራን በተለያዩ የትምህርት መስኮች እንዲመደቡለት ለትምህርት ሚኒስቴር የፍላጎት መግለጫ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም የተጠየቁትን ያህል መምህራን ሊመደቡለት አልቻሉም። ለነገሩ ይህ የፍላጎት ጥያቄ የቀረበው ዩኒቨርሲቲው ከሶስት ሺህ በላይ ተማሪዎችን ሊቀበል ይችላል በሚል እሳቤ ነበር። ዩኒቨርሲቲው በትምህርት ሚኒስቴር ከተመደቡለት መምህራን በተጨማሪ ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች በዝውውርና ከገበያም በቀጥር ለማሟላት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። እስከ ሰኔ 30/2004 ድረስ ስራ ላይ የነበሩት መምህራን ብዛት በየትምህርት ክፍሎቻቸው በሚከተለው ሰንጠረዥ የሚታየውን ይመስላል።

ሰንጠረዥ 5. በስራ ላይ ያሉ መምህራን

| S. No. | Department | Dip. (TA) | BA/BSc | | | MA/MSc | | | PhD | Total Academic Staff | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | M | F | T | M | F | Total | | M | F | T |
| 1 | Electrical Engineering (and Computer Science) | | 4 | 1 | 5 | 3 | | 3 | | 7 | 1 | 8 |
| 2 | Mechanical Engineering | | 1 | | 1 | 4 | | 4 | | 5 | | 5 |
| 3 | Chemical Engineering | | | | | 5 | | 5 | | 5 | | 5 |
| 4 | Civil Engineering | | | | | 3 | 1 | 4 | | 3 | 1 | 4 |
| 5 | Biology (and Biotechnology) | | 3 | | 3 | 8 | | 8 | | 11 | | 11 |
| 6 | Chemistry | | | | | 6 | | 6 | | 6 | | 6 |
| 7 | Mathematics (and Stat) | | 2 | | 2 | 12 | 1 | 13 | | 14 | 1 | 15 |
| 8 | Physics | | | 1 | 1 | 8 | | 8 | 1 | 9 | 1 | 10 |
| 9 | Accounting and Finance | | | 1 | 1 | 3 | | 3 | | 3 | 1 | 4 |
| 10 | Economics | | 3 | 3 | 6 | 4 | | 4 | 1 | 8 | 3 | 11 |
| 11 | Management | | 4 | | 4 | 3 | | 3 | | 7 | | 7 |
| 12 | English | | | | | 12 | | 12 | | 12 | | 12 |
| 13 | Civics | | 4 | 1 | 5 | 3 | | 3 | | 7 | 1 | 8 |
| 14 | Psychology | | | | 0 | 2 | | 2 | | 2 | | 2 |
| 15 | Agriculture | | | | | 3 | | 3 | | 3 | | 3 |
| 16 | Geography | | | | | 2 | | 2 | | 2 | | 2 |
| 17 | Chemistry (Technical Assistant) | | 2 | | 2 | | | | | 2 | | 2 |
| 18 | Biology (Technical Assitant) | | 3 | | 3 | | | | | 3 | | 3 |
| 19 | Computer TA | 1 | | | | | | | | 1 | | 1 |
| 20 | Medicine | | 1 | | 1 | 1 | | 1 | | 2 | | 2 |
| **Total** | | **1** | **27** | **7** | **34** | **82** | **2** | **84** | **2** | 112 | **9** | **121** |

እስከ ሰኔ 30/2004 ስራ ላይ የነበሩት የአካዳሚክ ሰራተኞች ብዛት 121 ሲሆን ከዚህ ውስጥ የሴቶች ቁጥር /7.5%/ በጣም አነስተኛ ነው። ከጠቅላላው የመምህራን ብዛት በጣም አብዛኛዎቹ በትምህርት ሚኒስቴር የተመደቡ ሲሆን የተወሰኑት በቅጥር እና በዝውውር የተገኙ ናቸው። በትምህርት ሚኒስቴር ከተመደቡት ውስጥ በስራ ያልተገኙ መምህራን አሉ፤ እነሱም ሁለት ከኤሌክትሪካል ምህንድስና /ቅድመ ምረቃ/፤ ሶስት በኬሚካል ምህንድስና /ሁለት ቅድመ ምረቃ እና አንድ ድህረ ምረቃ/፤ ሶስት በሲቪል ምህንድስና /ቅድመ ምረቃ/፤ አንድ በኢኮኖሚክስ /ቅድመ ምረቃ/፤ ሶስት በማኔጅመንት /ቅድመ ምረቃ/፤ እና አንድ በታሪክ /ድህረ ምረቃ/ በድምሩ 13 መምህራን ወይ ጭራሽ ሪፖርት ያላደረጉ ወይም ደግሞ ሪፖርት አድርገው ስራ ላይ ያልተገኙ ናቸው። ከዚሁም በተጨማሪ አንድ የሜካኒካል ምህንድስና መምህር /አቶ የማነ አለሙ/ ከድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ከአንድ የኛ መምህር ጋር በቅይይር ወደኛ ከተዛወረ በኋላ ለአንድ ወር ያህል ሪፖርት ካደረገ በኋላ በስራ ሊገኝ አልቻለም።

በርከት ያሉ መምህራን /በተለይ እጥረት ባለብን መስኮች/ ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች በዝውውር እንዲመጡ ደብዳቤ የፃፍንላቸው ቢሆንም እስካሁን የተሳካልን ግን የተወሰኑት ብቻ ነው። ከነዚህም ውስጥ አንድ በማኔጅመንት ሁለተኛ ዲግሪ ያለው /ከወለጋ ዩኒቨርሲቲ/ እና አንድ የኮምፕዩተር ቴክኒካል አሲስታንት ደግሞ ከአክሱም ዩኒቨርሲቲ ይገኙባቸዋል። በኬሚካል ምህንድስና መጀመርያ ተመድው የነበሩ መምህራን ሶስት ሲሆኑ /አንድ በድህረ ምረቃ ሁለት በቅድመ ምረቃ/ ከላይ እንደተጠቀሰው ሁለቱ ሊመጡ አልቻሉም። ሆኖም ከታህሳስ አንድ ጀምሮ 5 ተጨማሪ ድህረ ምረቃ የጨረሱ ስለተመደቡልን በዚሁ መስክ የነበረን እጥረት ተፈቶልናል። በአመቱ ከፍተኛ የመምህራን እጥረት ያጋጠመው በሲቪል ምህንድስና መስክ ሲሆን ቀደም ብለው ከተመደቡልን ሁለት መምህራን በተጨማሪ በአመቱ መጨረሻ አከባቢ ሁለት ተጨማሪ መምህራን ስለተመደቡልን እጥረቱ በመጠኑም ቢሆን ሊቃለል ችሏል።

የመምህራን ቅጥር ስራዎችን በተመለከተ ደግሞ የተወሰኑ መምህራን የቀጠርን ሲሆን እነሱም አንድ በሜካኒካል ኢንጂነሪንግ፤ ሶስት በአካውንቲንግ፤ አራት በኢኮኖሚክስና ሁለት ደግሞ በማኔጅመንት በድምሩ አስር መምህራን ቀጥረናል። በቴክኒካል ረዳትነት ደግሞ ሁለት በኬሚስትሪ ሶስት ደግሞ በባዮሎጂ በድምሩ አምስት ቴክኒካል ረዳቶችን ቅጥር አካሂደናል።

## 1.3. ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ተልእኮውን ለማሳካት ይቻለው ዘንድ ከሚያስፈልጉት ግብአቶች ውስጥ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ከዋነኞቹ ግብአቶች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው። የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት ዩኒቨርሲቲው በሚያከናውናቸው ስራዎች ስፋትና ጥልቀት እንዲሁም በሚቀበላቸው የተማሪዎች ብዛት የሚወሰን ሲሆን ዩኒቨርሲቲው ስራውን ለመጀመርና ለማካሄድ ያስፈልጉታል ተብለው በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የፀደቁለት በርከት ያሉ የስራ መደቦች አሉት። በተለይ የሰው ሃብት ልማት ማእከል እና የፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ሃላፊዎች በትምህርት ሚኒስቴር በተላከው መመርያ መሰረት ከሚመለከታቸው የአስተዳደር አካላት ጋር በመነጋገር የዝውውር ቅጥር የተከናወነ ሲሆን ለሌሎች የስራ መደቦች ደግሞ በህጉ መሰረት የቅጥር ስራዎችን በስፋት በማካሄድ በርከት ያሉ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ቀጥረናል። እስከ ሰኔ 30 ድረስ በቋሚነት 211 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን በኮንትራ ደግሞ 61 ሰራተኞችን በድምሩ 272 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ቀጥረናል። በሲቪል ሰርቪስ የፀደቁት የስራ መደቦች በድምሩ 380 ሲሆኑ ከዚህ ውስጥ 367 ቀደም ብለው የፀደቁት የስራ መደቦች ናቸው። 13 ደግሞ የግንባታ ስራዎችን ለመከታተል የሚያስችለን የምህንድስና ማስተባበርያ ፅ/ቤት ለማቋቋም ቆየት ብሎ ፀድቆ የተላኩልን የስራ መደቦች ናቸው። ለምህንድና ማስተባበርያ ፅ/ቤት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የክፍት ስራ ወጥቶ አመልካች ስላልተገኘ ለሁለተኛ ጊዜ በጋዜጣ ወጥቶ አሁንም አመልካች ሊገኝ ስላልቻለ ለሶስተኛ ጊዜ የደምወዝ ደረጃ በመጨመር /ደምወዙ ከተመደበው ደረጃ ውስጥ አምስት እርከን ገባ ብሎ/ ለመቅጠር የሚያስችለን ማስታወቅያ በጋዜጣ እንዲወጣ ተደርጎ የተወሰኑ አመልካቾች ተገኝተው ነበር። ሆኖም በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ተመሳሳይ ችግር በማጋጠሙ ምክንያት ፅ/ቤቱ በፕሮጀክትነት እንዲዋቀር የሚል አዲስ ማስተካከያ ሰኔ ወር ላይ የተላከ ስለሆነ በተላከው ማስተካከያ መሰረት ቅጥር ለማካሄድ የቅጥር ማስታወቅያ በጋዜጣ እንዲወጣ ተደርጓል። እስካሁን በፕሮጀክት ስራው ሲሰሩ ከቆዩ ሰራተኞችም /ዓዲግራት ቤቶች ልማት ኤጀንሲ የዩኒቨርሲቲ ግንባታ ክትትል/ መቅጠር እንደሚቻል በመመርያው ላይ የተጠቀሰ በመሆኑ በማስታወቅያው ከሚያመለክቱት እና አሁን ካሉት የፕሮጀክት ሰራተኞች እንደአስፈላጊነቱ እየታየ ቅጥር ይካሄዳል። የህንፃ ግንባታው ክትትል በዩኒቨርሲቲው በኩል ከ2005 ጀምሮ እንዲካሄድ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ርክክቡ ከተደረገ በኋላ ስራውን

ሙሉ ለሙሉ ዩኒቨርሲቲው ተረክቦ የሚያካሂደው ይሆናል። ለክትትሉ ይጠቅም ዘንድ በሲቨል ምህንድስና የተቀጠሩት መምህራንም ከማስተማር ስራቸው በተጨማሪ የግንባታ ክትትል እንዲያደርጉ የሚችሉበት ሁኔታም የሚታይ ይሆናል።

ሰንጠረዥ 6. የፀደቀልን መዋቅርና እስከ ሰኔ 30 ድረስ በቋሚነት የተቀጠሩ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች

| ተ.ቁ. | ፅህፈት ቤት | በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የፀደቀ ሰራተኛ ብዛት | ዘንድሮ በቋሚ ሰራተኛነት እንዲቀጠር የተወሰነ ብዛት | እስካሁን የተቀጠረ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | ፕረዚደንት ፅ/ቤት | 4 | 4 | 1 | 2 | 3 |
| 2 | እቅድና ተቋማዊ ማሻሻያ ፅ/ቤት | 7 | 3 | 2 | 2 | 4 |
| 3 | ሕዝንብና የውጭ ግንኙነት ፅ/ቤት | 4 | 2 | 1 | 1 | 2 |
| 4 | ውስጥ ኦዲት ፅ/ቤት | 4 | 3 | 3 | 1 | 4 |
| 5 | ስርኣተ ፆታ ፅ/ቤት | 3 | 2 | 1 | | 1 |
| 6 | ኣስተዳደርና ልማት ም/ፕረዚዳንት ፅ/ቤት | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 |
| 7 | ሰው ሃብት ልማት ማእከል | 10 | 5 | 4 | 3 | 7 |
| 8 | ኣካዳሚክና ምርምር ም/ፕረዚዳንት ፅ/ቤት | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 |
| 9 | ሬጂስትራር ፅ/ቤት | 13 | 11 | 2 | 5 | 7 |
| 10 | ቤተመፃህፍትና ኢንፎርሜሽን ማእከል | 26 | 17 | 6 | 7 | 13 |
| 11 | መሰረታዊ ኣገልግሎት ማእከል | 137 | 59 | 15 | 30 | 45 |
| 12 | ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ፋካልቲ | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 |
| 14 | ኢንጂነሪንግ ፋካልቲ | 2 | 2 | | 4 | 4 |
| 15 | ተፈጥሮ ሳይንስ ፋካልቲ | 2 | 2 | | 3 | 3 |
| 16 | ማህበራዊ ሳይንስ | | | | 1 | 1 |
| 17 | ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | | | | 2 | 2 |
| 16 | ህክምና ጤና ሳይንስ ፋካልቲ | 2 | 2 | | 2 | 2 |
| 17 | የፋይናንስ ኣስተዳደር ዳይሬክቶሬት | 16 | 14 | 6 | 5 | 11 |
| 18 | ግዥና ንብረት ኣስተዳደር ዳይሬክቶሬት | 10 | 10 | 6 | 3 | 9 |
| 19 | የተማሪዎች ዲን | 121 | 65 | 23 | 64 | 87 |
| 20 | የምህንድስና ማስተባበርያ ፅ/ቤት | 13 | 13 | | | |
| ድምር | | 380 | 220 | 73 | 138 | 211 |

ሰንጠረዥ 6 መዋቅር የፀደቀላቸው የስራ መደቦችና እስካሁን የተቀጠሩት የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት በየክፍሉ የሚያሳይ ሲሆን በአመቱ ይቀጠራሉ ተብሎ የተያዘው እቅድ ተግባራዊ እንደተደረገ ማየት ይቻላል።

## 1.4. የ2004 መደበኛ ባጀት አጠቃቀም

ለ2004 የባጀት ዘመን ለዩኒቨርሲቲው የተመደበለት የመደበኛ ባጀት መጠን ብር 26085728.00 የነበረ ሲሆን ተጨማሪ ባጀት እንዲፈቀድልን ባቀረብነው ጥያቄ መሰረት ለስራ ማስኬጃ 3282214.00 ለደምወዝ ደግሞ 1372985.58 በድምሩ ብር 4655199.58 ተጨማሪ ባጀት ተፈቅዶልናል። በዚሁም መሰረት ለአመቱ የተፈቀደልን ጠቅላላ ባጀት ብር **30740927.58** ነበር። በየሂሳብ መደቡ የተፈቀደልን ባጀት በተመለከተ ደግሞ በ6ወር እና በ9ወር ሪፖርት እንደተመለከተው የባጀት ማዘዋወር ስራዎች መሰራት ስለነበረባቸው የባጀት ዝውውሮችን ከአንድ የሂሳብ መደብ ወደ ሌላው በህጉ መሰረት አካሂደናል። በዚህመ ምክንያት በዚሁ ሪፖርት በሚቀጥለው ሰንጠረዥ በየሂሳብ መደቡ የተቀመጠው እና ቀደም ብሎ በተዘጋጁት የሩብ አመት ሪፖርቶች የተቀመጡት መጠኖች ልዩነት እንዳላቸው ማየት ይቻላል። በአመቱ ውስጥ በርካታ የቀጥታና የፕሮፎርማ ግዥዎች እንዲሁም የተወሰኑ ውስን ጨረታዎችና ሁለት ግልፅ ጨረታዎች በማካሄደ በርካታ እቃዎች ተገዝተዋል።

ከታች በሰንጠረዥ 7 የተቀመጠው የባጀት አጠቃቀመ ዝርዝር እስከ ሰኔ 30 ያለውን የባጀት አጠቃቀማችን የሚያመለከት ነው። ስለዚህ እስከ ሰኔ 30 ወጪ የተደረገው መጠን ብር 24527622.24 ሲሆን መጀመርያ ተፈቅዶልን ከነበረው ባጀት /ማለትም ብር 26085728.00 ጋር ሲነፃር የባጀቱን **94%** ተጠቅመንበታል። ሆኖም ተጨማሪ ተጨማሪ ክፍያዎችን ለማድረግ ከተጨመረልን ባጀት ጋር ሲታይ ግን በድምሩ የተፈቀደልን ባጀት ብር **30740927.58** ስለሆነ የባጀት አጠቃቀማችን **80%** እንደሆነ ያሳያል። ተጨማሪ ባጀት የጠየቅነው በግልፅ ጨረታ ወጥተው በጊዜው ይደርሱልናል ብለን ውለታ የገባንላቸው ማቴርያሎች /ለምሳሌ 120 ዴስክቶፕ እና 20 ላፕቶፕ ኮምፕዩተሮች/ በባጀት አመቱ ገቢ ያልተደረጉ ስለሆነ ክፍያው ሊፈፀም አልቻለም። በዚሁም ምክንያት ፈሰስ የተደረገው ባጀት ብር 6213305.34 ሆኗል። በአጠቃላይ ሲታይ ግን የባጀት አጠቃቀማችን አጥጋቢ ነበር ተብሎ ሊቀመጥ ይችላል።

ሰንጠረዥ 7፡ የ2004 ባጀት አጠቃቀም

| የሂሳብ መደብ | መግለጫ | 1. ለፕሮግራም አንድ የተፈቀደ | 2. ለፕሮግራም ሁለት የተፈቀደ | 3. ጠቅላላ የተፈቀደ (1+2) | 4. እስከ ሰኔ 30 2004 የተከፈለ | 5. ቀሪ ባጀት (3-4) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6111 | ለቋሚ ሰራተኞች ደምወዝ | 3011234.88 | 3069038.2 | 6080273.08 | 6066899.28 | 13373.80 |
| 6113 | ለኮንትራት ሰራተኞች ምንዳ | 199832 | | 199832.00 | 169901.25 | 29930.75 |
| 6114 | ለቀን ሰራተኞች ምንዳ | 53187.6 | | 53187.60 | 38556.26 | 14631.34 |
| 6115 | ለውጭ የኮንትራት ሰራተኞች ምንዳ | | | 0.00 | | 0.00 |
| 6116 | ለሰራተኞች የሚደረጉ የተለያዩ ክፍያዎች | | | 0.00 | | 0.00 |
| 6121 | ለቋሚ ሰራተኞች አበል | 670249 | | 670249.00 | 668477.83 | 1771.17 |
| 6131 | ለቋሚ ሰራተኞች ጡረታ መዋጮ | 216029.16 | 214832.67 | 430861.83 | 430263.25 | 598.58 |
| 6211 | ለደንብ ልብስ ለልብስ ለፍራሽና አልጋ ልብስ | 398250 | | 398250.00 | 341476.18 | 56773.82 |
| 6212 | ለአላቂ የቢሮ እቃዎች | 3927411 | | 3927411.00 | 3238840.42 | 688570.58 |
| 6213 | ለህትመት | 291599 | | 291599.00 | 154524.08 | 137074.92 |
| 6214 | ለአላቂ የህክምና እቃዎች | 184835 | | 184835.00 | 155484.57 | 29350.43 |
| 6215 | ለአላቂ የትምህርት እቃዎች | | 252610 | 252610.00 | 248567.43 | 4042.57 |
| 6216 | ለምግብ | 3796002.9 | | 3796002.90 | 3366651.61 | 429351.29 |
| 6217 | ለነዳጅና ቅባቶች | 513151 | 116 | 513267.00 | 513151 | 116.00 |
| 6218 | ለሌሎች አላቂ እቃዎች | 453760 | | 453760.00 | 348087.71 | 105672.29 |
| 6219 | ለተለያዩ መሳርያዎችና መፃህፍት | 722915.22 | | 722915.22 | 500832.52 | 222082.70 |
| 6221 | ለግብርና ለደንና ለባህር ግብአቶች | | | 0.00 | | 0.00 |
| 6222 | ለእንስሳት ህክምና የሚያገለግሉ | | | 0.00 | | 0.00 |
| 6223 | ለምርምርና ለልማት አላቂ እቃዎች | | 523165.08 | 523165.08 | 517270.44 | 5894.64 |
| 6231 | ለውሎ አበል | 639578 | 45213 | 684791.00 | 372720.78 | 312070.22 |
| 6232 | ለትራንስፖርት ክፍያ | 314340 | | 314340.00 | 250440.98 | 63899.02 |
| 6233 | ለመስተንግዶ | 164447 | | 164447.00 | 154086.65 | 10360.35 |
| 6241 | ለተሽከርካሪዎችና ለሌሎች መጓጓዣዎች እድሳትና ጥገና | 372172.04 | | 372172.04 | 366946.11 | 5225.93 |
| 6243 | ለፕላንት ለማሽነሪና ለመሳርያ እድሳትና ጥገና | 45000 | | 45000.00 | 16183.94 | 28816.06 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6244 | ለህንፃ ለቁሳቁስና ለተገጣጣሚዎች | | | 0.00 | | 0.00 |
| 6251 | በውል ለሚፈፀሙ የሙያ አገልግሎቶች | 12450 | | 12450.00 | 12450 | 0.00 |
| 6252 | ለኪራይ | 419963 | | 419963.00 | 381114.25 | 38848.75 |
| 6253 | ለማስታወቅያ | 137179.5 | 43529.28 | 180708.78 | 180708.78 | 0.00 |
| 6254 | ለመድን ዋስትና | 221441 | | 221441.00 | 220676.36 | 764.64 |
| 6255 | ለጭነት | 156919 | | 156919.00 | 62628 | 94291.00 |
| 6256 | ለአገልግሎች ክፍያዎች | 67500 | 25650 | 93150.00 | 92952.96 | 197.04 |
| 6257 | ለኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ | 515885.43 | | 515885.43 | 348807.52 | 167077.91 |
| 6258 | ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎች ክፍያ | 143013 | | 143013.00 | 143013 | 0.00 |
| 6259 | ለውሃ ፖስታና ሌሎች አገልግሎት ክፍያዎች | 332869 | | 332869.00 | 261957.9 | 70911.10 |
| 6271 | ለአገር ውስጥ ስልጠና | 600 | | 600.00 | | 600.00 |
| 6272 | ለውጭ አገር ስልጠና | | | 0.00 | | 0.00 |
| 6313 | ለፕላንት ለማሽነሪና ለመሳርያ መግዣ | 7586359.62 | | 7586359.62 | 4055452.88 | 3530906.74 |
| 6314 | ለህንፃ ለቁሳቁስ እና ተገጣጣሚዎች መግዣ | 923600 | | 923600.00 | 773594.26 | 150005.74 |
| 6315 | ለቀንድ ከብቶችና ለመጓጓዣ የሚውሉ | | | 0.00 | | 0.00 |
| 6412 | ለተቋሞችና ድርጅቶች እርዳታና መዋጮ ድጎማ | | | 0.00 | | 0.00 |
| 6417 | ለግለሰቦች እርዳታና ስጦታ | 75000 | | 75000.00 | 74904.04 | 95.96 |
| **ጠቅላላ ድምር** | | **26566773.35** | **4174154.23** | 30740927.58 | **24527622.24** | 6213305.34 |

የፋይናንስ ኦዲት ስራዎች በተመከተ ደግሞ እስከ ሶስተኛው ሩብ አመት ኦዲት የተደረገ ሲሆን በተለይ በባጀቱ የመጀመርያው ግማሽ አመት ታይተው የነበሩ ጥቃቅን ጉድለቶች እንዲስተካከሉ ተደርገዋል። የፋይናንስ ስራችን ባጠቃላይ በመንግስት ህግና ደንብ መሰረት እየተሰራ መሆኑን የውስጥ ኦዲት ሪፖርተ ያመለከተ ሲሆን መስተካከል ያለባቸው ነገሮችም ተቀምጠው ውይይት ተደርጎባቸዋል። የኦዲት ሪፖርቱን መሰረት በማድረግ ዳይሬክቶች፤ ዲኖች፤ የፋይናንስ አስተዳደር እና የግዥና ንብረት አስተዳደር ሰራተኞች በሙሉ የተገኙበት የግማሽ ቀን የኦዲት ኮንፈረንስ መጋቢት 28/2004 ተደርጓል። የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ካውንስልም የኦዲት ሪፖርቱንና የኦዲት ኮንፈረንሱን መሰረት በማድረግ ውይይት አካሂዶ ውሳኔ መሰጠት ባለባቸው ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ሰጥቶባቸዋል።

## 2. የአመቱ እቅድ አፈፃፀም

ከሐምሌ 1/2003 እስከ መጋቢት 30/2004 ባሉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ በዩኒቨርሲቲው የተከናወኑት ዋና ዋናዎቹ ተግባራት ከእቅዱ ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### ግብ 1. ለመጀመርያ ጊዜ አዲስ ተማሪዎችን ለመቀበል አስፈላጊ ዝግጅቶችን በማድረግ ትምህርት መጀመር

በዚህ ዋና ግብ ስር ከተሰሩት ዝርዝር ስራዎች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉትን ይመስላሉ፤

- *የግንባታ ስራዎች፤ የመሰረተ ልማት ስራዎች እና ለህንፃው አስፈላጊ የሆኑት ፈርኒቸሮችና ሌሎች ማቴርያሎች አቅርቦት በተመለከተ ክትትል ማድረግ*

የዩኒቨርሲቲው ግንባታ ያለበት ደረጃ በተመለከተ እስካሁን የመጀመርያው ምእራፍ አንድ አራተኛው ክፋይ የያዘው 12 ብሎኮች ተጠናቀው ከህዳር 24 ጀምሮ ጥቅም ላይ ውለዋል። በዩኒቨርሲቲው የተመደቡት ተማሪዎች ህዳር 24 እና 25 እንዲገቡ በቴሌቪዥን በተነገረው ማስታወቅያ መሰረት ወደ ግቢው የገቡ ሲሆን የተጠቀሱት ህንፃዎች ጥቅም ላይ መዋል የጀመሩት ተማሪዎቹን ከተቀበልንባቸው ቀናት ጀምሮ ነው። የህንፃዎች ግንባታ ለጥቅም ዝግጁ የሆኑት ተማሪዎች ሊገቡ ጥቂት ቀናት እስኪቀረው ድረስ ስለነበር መደበኛ የህንፃ ርክክብ ሳይደረግ ነው ተማሪዎቹ ገብተው ህንፃዎቹ ጥቅም ላይ መዋል የጀመሩት። የመጀመርያው ምእራፍ ሶስት አራተኛው ክፋይ 36 ብሎኮችን የሚያጠቃልል ሲሆን እስከ ሰኔ መጨረሻ ድረስ ግንባታው ከ90% በላይ ተጠናቋል። እስከ ነሐሴ 2004 መጨረሻ ላይ ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ በሚቀጥለው አመት ተማሪዎችን ለመቀበል ይደርሳል ብለን እየተጠባበቅን ነው። ህንፃዎቹ ይደርሳሉ በሚል እሳቤ ለ2005 የምንቀበላቸው አዲስ ተማሪዎች ብዛት 3260 እንደሆነ ለትምህርት ሚኒስቴር አሳውቀን በዚሁም መሰረት ዝግጅቶችን በማድረግ ላይ እንገኛለን። በሶስት አራተኛው ክፋይ በመሰራት ላይ ካሉት ከህንፃዎቹ ውስጥ የተማሪዎች ላውንጅ፤ የተወሰኑ የማስተማርያ ህንፃዎች እና የሌክቸር ትያትር /ሁለት ትያትሮች የያዘ አንድ ብሎክ/ በጣም ዘግይተው የነበረ ቢሆንም በተደረገው ክትትል ምክንያት ከተማሪዎች ላውንጅ ውጭ ሌሎቹ ጥሩ እንቅስቃሴ እየታየባቸው ስለሆነ እንደሚደርሱ እንጠብቃለን። የተማሪዎች ላውንጅ ግን ምንም እንቅስቃሴ እየተደረገበት ስላልሆነ እንደማይደርስ ከወዲሁ የታወቀ ሆኗል።

የሶስት አራተኛው የግንባታ ሂደቱን በተመለከተ ከኮንትራክተሮች ከቤቶች ልማት ኤጀንሲ እና ከገሬታ ኮንሳልታንት ጋር ተደጋጋሚ የሆኑ ግንኙነቶችን በማድረግ የክትትል ስራዎች ተሰርተዋል። የተሻለ ሊባል የሚችል ውጤትም ታይቶበታል። በመገንባት ላይ ካሉት 36 ብሎኮች ውስጥ በሃት ኮንስትራክሽን በመገንባት ላይ ያሉት የላይብረሪ እና የዲፓርትመንት ፅ/ቤት ብሎኮች ከፍተኛ የአሰራር ችግር ስላጋጠማቸው የኮንሳልታንቱ ስትራክቸራል ኢንጂነር ከአዲስ አበባ ድረስ መጥቶ እንዲያያቸው ተደርጎ ችግሮቹ በኮንትራክተሩ በኩል የአሰራር ጉድለቶች በመደረጋቸው ምክንያት የተፈጠሩ መሆናቸውን አስቀምጦ እንዴት መስተካከል እንዳለባቸውም አመላክቷል። ከክልል ኮንስትራክሽን ቢሮ የመጡ መሃንዲሶችም እንዲያዩዋቸው ተደርጎ አስተያየታቸውን ሰጥተውበታል። ለኮንትራክተሩ ማስጠንቀቅያ የተሰጠው ከመሆኑም በተጨማሪ ቦታውን ይከታተል የነበረውም አማካሪ መሃንዲስ ከቦታው ተነስቶ ወደ ቢሮ ስራ እንዲዛወር ተደርጓል። ችግር የነበረበት የላይብረሪው ክፍል እንዲፈርስ ተደርጎ በተቀመጠለት ማስተካከያ መሰረት ተሰርቷል።

የመሰረተ ልማት ስራዎች በተመለከተ የውሃና ፍሳሽ መስመሮች የተዘረጉ ሲሆን ውሃ ለዩኒቨርሲቲው ተብለው ከተቆፈሩት ሶስት ጉድጓዶች ውስጥ ከአንደኛው ጉድጓድ በጀነሬተር አመካኝነት በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ወደተሰራው ሪዘርቫየር /ታንከር/ እየደረሰ ነው። ከሪዘርቫየሩም ወደተለያዩ ቦታዎች መስመሮች ተዘርግተው በተከታታይነት እንዲደርስ እየተደረገ ነው። የውሃ አቅርቦት በጥሩ ሁኔታ ያለ ሲሆን የውሃ ችግር እስካሁን አላጋጠመንም፤ በዚህም በዩኒቨርሲቲው ጥሩ የውሃ አገልግሎት እየተሰጠ ስለሆነ ዩኒቨርሲቲው ደስተኛ ነው። ሆኖም ውሃውን ወደ ሪዘርቫየሩ ፓምፕ የሚደረገው በተገጠመው ጀነሬተር ስለሆነ ጀነሬተሩ ከተበላሸ አቅርቦቱ ስለሚቆም በአንድ በኩል ትራንስፎርመር መገጠም ያለበት ሲሆን በሌላ በኩልም ከሌሎቹ ጉድጓዶች ደግሞ ውሃ ወደ ሪዘርቫየሩ የሚደርስበት መንገድ መፈለግ አለበት። በዚሁም መሰረት አስፈላጊው ክፍያ ለክልሉ መብራት ሃይል ተፈፅሞ የውሃ ትራንስፎርመሩ የተገጠመ ሲሆን አገልግሎት መስጠት ግን ገና አልጀመረም። መሟላት ያለባቸው ነገሮች ተሟልተው በቅርቡ ስራ የሚጀምር ይሆናል።

የከተማው ውሃ አቅርቦት ፅ/ቤት ደግሞ የውሃ አቅርቦቱን ስራ ራሱ ፅ/ቤቱ እንዲሰራውና ዩኒቨርሲቲው ደግሞ በቆጣሪ ንባብ መሰረት እንዲከፍል የሚደረግበት አሰራር መከተል እንደሚያስፈልግ ጥያቄ አቅርቦልን ጥያቄውን በተመለከተ የዩኒቨርሲቲው ቦርድ በጥር 25 ስብሰባው አይቶ ወደ ከተማው ውሃ አቅርቦት ፅ/ቤት የማስተላለፉ ጉዳይ ጠቃሚ ቢሆንም ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር ተጨማሪ ውይይት ተደርጎበት ስምምነት ላይ እስኪደረስ ድረስ ለጊዜው ባለበት እንዲቆይ የሚል ውሳኔ ሰጥቶበታል። ወደ ውሃው ክሎሪን የመጨመር ስራ ግን ከከተማው የውሃ አቅርቦት ፅ/ቤት ጋር በመተባበር እየተሰራ ይገኛል።

የውስጥ ለውስጥ መንገድ ስራን /የኮብልስቶን ንጣፍ/ በተመለከተ በዲዛይኑ ላይ በተነሳው ጥያቄ መሰረት ዘግይቶ የነበረ ቢሆንም አሁን ግን ስራው ወደ መጠናቀቅ ደረጃ ደርሷል። በዲዛይኑ ላይ ተነስቶ የነበረው ጥያቄ የሚከተለውን ይመስላል። በዲዛይን የተቀመጠው ድንጋዩ የሚነጠፍበት ቦታ ቀይ አፈር /Red Ash/ ወይም ደግሞ አሸዋ ላይ እንዲሆን የሚያስቀምጥ ሲሆን በአንድ በኩል በአከባቢው ላይ ቀይ አፈር የሌለ በመሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ አሸዋ ላይ ቢነጠፍ ጥራት የሌለው በመሆኑ በክልሉ ከተሞች በመሰራት ባለበት መልኩ የድንጋይ ንጣፉ በተፈጨ ጥቁር ድንጋይ (00 ጠጠር) ላይ እንዲሆን ጥያቄ ለትምህርት ሚኒስቴር ቀርቦ በቅርቡ መልስ ተሰጥቶበት በ00 ጠጠር እንዲሰራ ተደርጓል። የውስጥ ለውስጥ መንገድ ስራ በመዘግየቱ ምክንያት በዩኒቨርሲቲው ግቢ ልናደርግ ያሰብነው የተከላ ስራ እንዲዘገይ የተደረገ ቢሆንም ከሰኔ 2004 ጀምሮ የተከላ ስራዎች በመሰራት ላይ ይገኛሉ።

ከህንፃዎች ግንባታ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ለዩኒቨርሲቲው የሚያገለግሉ የተለያዩ ማቴርያሎች የማሟላት ጉዳይ ነው። በዚሁም መሰረት በርከት ያሉ ማቴርያሎች /ፍራሾች፤ ወንበሮች፤ አልጋዎች፤ ጠረጴዛዎች/ ቀደም ብሎ በትምህርት ሚኒስቴር አመካኝነት በታሰረው ኮንትራት መሰረት ደርሰውን እየተጠቀመንባቸው እንገኛለን። በተለይ ወንበሮች እና ፍራሾች ለ2004 ከሚያስገልገን መጠን በላይ ስለመጡልን መጠነኛ የሆነ የስቶር ችግር ያጋጠመን ቢሆንም ለ2005 የትምህርተ ዘመን የሚያስፈልጉን የፍራሽ፤ የአልጋ፤ የትራስ እና የወንበር አቅርቦት ካለን ስቶክ መጠቀም ስለምንችል ከወዲሁ ችግሩን አቀሎልናል። ቀደም ብለው በትምህርት ሚኒቴር አመካኝነት ውለታ ከተገባቸው እቃዎች በተጨማሪ ዩኒቨሪሲቲው በርካታ ግዥዎችን በማድረግ ለማሟላት ጥረት ተደርጓል።

ለተማሪዎች ምግብ ዝግጅት በተመለከተ ቀደም ብለው በትምህርት ሚኒስቴር አመካኝነት ውል የተገባባቸው ማቴርያሎች /ብረት ድስቶች፤ ጭልፋዎች፤ የስጋና የሽንኩርት መፍጫ ማሽኖች፤ ክፍልፋይ ትሪዎች፤ ማንኪያና ሹካ፤ የስጋና ሽንኩርት መክተፍያ፤ የፕላስቲክ በርሚሎች ወዘተ/ ደርሰውን ጥቅም ላይ ውለዋል። ሌሎች ተጨማሪ ማቴርያሎች /ለምሳሌ የፕላስቲክ በርሚሎች /የትምህርት ሚኒስቴር ከመድረሱ በፊት/፤ የሻይ ኩባያዎች፤ ፍሪጆች ወዘተ/ ደግሞ በራሳችን ገዝተን አሟልተን እየተጠቀምንባቸው እንገኛለን። በኤሌክትሪክ የሚሰሩ የወጥ መስሪያ ምድጃዎች እና ሌሎች የኪችን መሳርያዎች ዘግይተው የደረሱን ቢሆንም ገና ስላልተገጠሙ ጥቅም ላይ ገና አልቃሉም። ሆኖም ግን የማቀዝቀዣ ክፍል /Cold Room/ በጊዜው ደርሶ ተገጥሞ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። የምድጃዎቹ በወቅቱ አለመድረስና ስራ አለመጀመር በመኖሩ ምክንያት በእንጨት የሚሰራ አማራጭ መፈለግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በዚሁም መሰረት በቆርቆሮ ሁለት ቤቶችን /አንድ ለወጥ መስሪያ አንድ ደግሞ ለእንጀራ መጋገርያ/ እንዲሰራ ተወስኖ የአንድ አራተኛ የህንፃውን ክፋይ በሰሩት ተቋራጮች መሃከል ውሱን ጨረታ ወጥቶ የሚሰራው ተለይቶ ውል ተፈርሞ ስራው ተሰርቶ የወጥ እና የእንጀራ ቤቶቹ አገልግሎት ላይ ውለዋል። የቆርቆሮ ቤቶችን መስራታችን ለእንጀራ መጋገር እና የወጥ ስራ ወሳኝ አስተዋፅኦ አድርጎልናል፤ እነሱ ባይሰሩ ኖሮ ጭራሽ ተማሪዎችን መቀበል አንችልም ነበር።

የሁለተኛው ዙር ግንባታ በርካታ ሀንፃዎችን ያካተተ ሲሆን የዝግጅት ምእራፎች ተጠቃለው /ኮንትራክተሮች ተመርጠው ስልጠና ተሰጥቷቸው ውል ተፈርሞ ቅድመ ክፍያ በአብዛኛው ተፈፅሞ/ የግንባታ ስራዎች ሰኔ 2004 ላይ በተወሰነ መልኩ ተጀምረዋል። በሁለተኛው ዙር እንዲገነቡ የተመደቡት ህንፃዎች ጠቅላላ ብዛት 68 ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 5 የልብስ ማጠብያ ገንዳዎችን እና 9 የትራንስፎርመር ቤቶችን እንደተጨማሪ ህንጫዎች ወስደን **የሁለተኛው ዙር የዋና ዋና ብሎኮች ብዛት 54 ይሆናል።** የሁለተኛው ዙር ግንባታ በ2004 መጨረሻ ላይ መጀመሩ ህንፃዎቹ ለ2006 ሰለሚደርሱ በርከት ያሉ ተማሪዎችን ለመቀበል ያስችለናል። ከታች በሰንጠረዥ ከተቀመጡት ውስጥ የcommercial complex (ክሊኒክ እና ሌሎች አገልግሎቶችን የሚይዝ ብሎክ) ስራ ቀደም ብሎ የተጀመረ ሲሆን በትራንስፎርመር ቤት ከተቀመጡት ዘጠኝ ህንፃዎች ውስጥ ሶስቱ ቀደም ብለው ተጀምረው ተገባደዋል የተቀሩት ስድስቱ በዩለተኛው ዙር የሚሰሩ ይሆናሉ። የሁለተኛ ዙር ብሎኮች ብዛት፤ የተመደቡ ስራ ተቋራጮች ዝርዝር እያ የተመደበው ባጀት በሚከተለው ሰንጠረዥ የተቀመጠውን ይመስላል፤

## ሰንጠረዥ 8፡ የሁለተኛ ዙር ግንባታ ብሎኮች፤ የተመረጡ የስራ ተቋራጮችና የተያዘለት ባጀት

| ተ.ቁ | የስራ ተቋራጩ ደረጃ | የስራ ተቋራጩ ስም | ብሎክ አይነት | ብሎክ ኮድ | ብዛት | የኮንትራት መጠን /ብር/ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 5 | Goitom W/gebriel Construction | Dinning Type 2 | DN-T2-16 | 1 | 21,554,537.78 |
| | | | Kitchen Type 1 | KI-T1-17 | 1 | |
| | | | Auditorium | AM-T1-XX-19 | 1 | |
| 2 | 5 | Mulugeta Tadesse B.C | Dormitory with TV | DO-T1/TV-222 | 1 | 14,599,981.59 |
| | | | Dormitory with TV | DO-T1/TV-223 | 1 | |
| 3 | 3 | Teklu W/Miceal B.C | Dormitory court yard type | Do-CYT-T1-231 | 1 | 18,633,479.46 |
| | | | Dormitory with TV | DO-T1/TV-225 | 1 | |
| 4 | 3 | Niat Construction B.C | Dormitory court yard type | Do-CYT-T1-230 | 1 | 18,633,479.46 |
| | | | Dormitory with TV | DO-T1/TV-232 | 1 | |
| 5 | 4 | H/Mariam Hiluf B.C | Dormitory with TV | DO-T1/TV-233 | 1 | 14,599,981.59 |
| | | | Dormitory with TV | DO-T1/TV-234 | 1 | |
| 6 | 6 | Gizen G.C | Dormitory with TV | DO-T1/TV-228 | 1 | 14,599,981.59 |
| | | | Dormitory with TV | DO-T1/TV-229 | 1 | |
| 7 | 3 | kalka Construction | Dormitory with TV | DO-T1/TV-200 | 1 | 14,599,981.59 |
| | | | Dormitory with TV | DO-T1/TV- | 1 | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 263 | | |
| 8 | 4 | Solomon Abraha Gebru | Labaratory type 1 | LAB-T1-143 | 1 | 14,466,841.24 |
| | | | Labaratory type 1 | LAB-T1-144 | 1 | |
| 9 | | Amanuel Gedlu Biyadglighn | Labaratory type 1 | LAB-T1-145 | 1 | 14,466,841.24 |
| | | | Labaratory type 1 | LAB-T1-146 | 1 | |
| 10 | 5 | Kahsay Atsbaha Abraha | Labaratory type 1 | LAB-T1-142 | 1 | 13,166,970.69 |
| | | | Class room | CL-D1-149 | 1 | |
| 11 | | Brothers Engineering | Small central library | LI-T1-100 | 1 | 9,935,485.73 |
| 12 | | Kibrom Desta G/her | Dormitory court yard type | Do-CYT-T1-201 | 1 | 11,333,488.67 |
| 13 | | Welday Haylu wuneh | Dormitory court yard type | Do-CYT-T1-203 | 1 | 11,333,488.67 |
| 14 | 6 | H/Miceal Desta T/Haymanot | Labaratory type 1 | LAB-T1-166 | 1 | 7,758,301.24 |
| | | | Washing basin | LN-T1-358 | 1 | |
| 15 | | Haftom W/Gebriel G/Cherkos | Labaratory type 1 | LAB-T1-171 | 1 | 7,758,301.24 |
| | | | Washing basin | LN-T1-359 | 1 | |
| 16 | | Tsigabu G/Slassie H/Miceal | Labaratory type 1 | LAB-T1-172 | 1 | 7,758,301.24 |
| | | | Washing basin | LN-T1-360 | 1 | |
| 17 | | Daniel kiros A/Mariam | Labaratory type 1 | LAB-T1-140 | 1 | 7,758,301.24 |
| | | | Washing basin | LN-T1-367 | 1 | |
| 18 | | Abrahaley Belay Gebeyuh | Labaratory type 1 | LAB-T1-141 | 1 | 7,758,301.24 |
| | | | Washing basin | LN-T1-366 | 1 | |
| 19 | | Getachew & Zelalem Tadesse T/Hiwot | Seminar | SE-M1-150 | 1 | 9,137,811.97 |
| | | | Teachers Lounge | TL-T1-106 | 1 | |
| 20 | | Kassahun Mehari H/Slassie | Seminar | SE-M1-151 | 1 | 9,261,403.39 |
| | | | Student Lounge | SL-T1-107 | 1 | |
| 21 | | Nebyu kiros A/Mariam | Seminar | SE-M1-152 | 1 | 10,307,038.52 |
| | | | Lecture Hall | LH-D1-104 | 1 | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 22 | | Aklilu Asefa G/Kidan | Seminar | SE-M1-153 | 1 | 7,646,895.33 |
| 23 | | Mekonnen W/Rufeal Asfaw | Decentralized Adminstration | DAB-T2-102 | 1 | |
| | | | Lecture Hall | LH-D1-103 | 1 | 7,404,837.57 |
| 24 | | Kibralem Mebrahtu Bru | Department head | DHB-T2-101 | 1 | |
| | | | Lecture Hall | LH-D1-105 | 1 | 7,269,008.31 |
| 25 | 6 | Yared Mehari G.C | Commercial complex | CC-T1-XX-12 | 1 | |
| | | | Bread Bakery | BA-T2-22 | 1 | |
| | | | Injera Bakery | BA-T1-21 | 1 | 8,112,323.51 |
| 26 | 3 | United Construction P.L.C B.C | Transformer Houses | TR-T1 | 9 | |
| 27 | 4 | Tadelle Berhe B.C | Dormitory with TV | DO-T1/TV-226 | 1 | |
| | | | Work Shop | WS-T1-164 | 1 | 10,002,055.90 |
| 28 | 6 | Brhane G/Mariam GC & WC | Labaratory type 1 | LAB-T1-167 | 1 | |
| | | | Work Shop | WS-T1-165 | 1 | 9,935,485.73 |
| 29 | 6 | Belay Negash G/Slassie G.C | Class room | CL-D1-154 | 1 | |
| | | | Work Shop | WS-T1-162 | 1 | 8,635,615.18 |
| 30 | 4 | Ataklti Belay Fantu B.C | Dormitory with TV | DO-T1/TV-216 | 1 | 7,299,990.79 |
| 31 | 5 | Araya Wube G.C | Dormitory with TV | DO-T1/TV-202 | 1 | 7,299,990.79 |
| 32 | 3 | Nigus Aynimishet B.C | Dormitory with TV | DO-T1/TV-227 | 1 | 7,299,990.79 |
| 33 | 3 | Fantaye Gidey G/Yesus B.C | Dormitory with TV | DO-T1/TV-235 | 1 | 7,299,990.79 |
| 34 | 5 | Teklebrhan Tadesse G/Medhin B.C | Dormitory with TV | DO-T1/TV-262 | 1 | 7,299,990.79 |
| Total | | | | | 68 | 354,928,474.86 |

- የሰው ሃይል ቅጥሮችን ማከናወን

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ተልእኮውን ለማሳካት የሰው ሃብት ወሳኝ ተራ እንደሚጫወት እሙን ነው። ዩኒቨርሲቲው ስራውን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ከሰራቸው ስራዎች በዋነኛነት ሊጠቀስ የሚችለው በሰው ሃብት ራሱን ማጠናከር ነው። በዚህም መሰረት እስከ ሰኔ 30 ድረስ በአካዳሚክ ዘርፉ ዩኒቨርሲቲው በምደባ፤ በቅጥር እንዲሁም በዝውውር ያገኛቸው 121 የአካዳሚክ ሰራተኞች አሉት። የሰራተኞቹ ደምወዝ በባንክ መክፈል ከህዳር ወር ጀምሮ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን ለመምህራን መከፈል የሚገባው የቤት አበል ዘግየት ብሎ የተጀመረ ቢሆንም በአግባቡ እየተከፈለ ይገኛል። የመምህራን የቤት አበል ክፍያን በተመለከተ ቀደም ብሎ የአዲስ ዩኒቨርሲቲ ሃላፊዎች ጥያቄውን ለትምህርት ሚኒስቴር አቅርበው ስለነበር ጉዳዩ በኮሚቴ ታይቶ ፕሮፖዛል እንደሚቀርብ መልስ ተሰጥቶበት ነበር። የዩኒቨርሲቲው መምህራን ስለአበሉ በተደጋጋሚ ጥያቄ ያቀረቡ መሆናቸው ማስቀመጥ ተገቢ ነው። በዚሁም መሰረት የዩኒቨርሲቲው ቦርድ ህዳር 15/2004 ባደረገው ስብሰባ ስለ የመምህራን ቤት አበል ጉዳይ ተወያይቶ የአክሱምን ዩኒቨርሲቲ ልምድ በመውሰድ ውሳኔ አስተላልፎበት የነበረ መሆኑን ማስታወስ ተገቢ ነው። በመጨረሻም በትምህርት ሚኒስቴር በኩል በአግባቡ መልስ ተሰጥቶበት የቤት አበል ክፍያው በመከፈል ላይ ይገኛል።

የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በተመለከተ ደግሞ 211 ቋሚ እና 61 የኮንትራት ሰራተኞች በድምሩ 272 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ተቀጥረዋል። የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ቅጥር የተካሄደው በፈተና ውድድር ሲሆን የቅጥሩን ስራ የሚያካሂድ በዩኒቨርሲቲው ሰው ሃብት ልማት ማእከል ዳይሬክተር የሚመራ አምስት መምህራን ያሉት ኮሜቴ /የኮሜቴው አባላት ሃፍቱ ሃይሉ፣ ደስታ ገበያ፣ ኢሳያስ ወልደትንሳኤ፣ ሊላይ ፈረደ፣ ጠዓመ አብርሃ፣ ፃድቅ ኪዳነማርያም/ የተቋቋመ ሲሆን ኮሚቴው እንደየስራው አይነት ፈተና ራሱም እያዘጋጀ አስፈላጊ ከሆነም ከሚመለከታቸው ባለሞያዎች ድጋፍ እያገኘ /ከዩኒቨርሲቲው ውጭም/ ቅጥሮችን አካሂዷል። ፈተናው ፍትሃዊነት ባለው መልኩ እንዲካሄድም ኮሚቴው ፈተናውን በጋራ በፈተናው እለት አዘጋጅቶ ወድያውኑ እንዲፈተኑት እና ውጤታቸውም በፍጥነት እንዲያውቁት አድርጓል። ቅሬታ አቅራቢ ካለም ወደኮሚቴው ቀርቦ መልስ ያገኛል። ባጠቃላይ የቅጥር ስራው በጥሩ ሁኔታ የተካሄደ ቢሆንም ያጋጠመ ችግርም ነበር። የአስተዳደር ሰራተኞችን በተመለከተ ያጋጠመው ችግር የአትክልተኞችን ቅጥር የሚመለከት ሲሆን የዩኒቨርሲቲው ፐርሶኔል ሁለት የቅርብ ቤተሰቦቹ /አንድ እህትና አንድ ወንድም/ በፈተናው ላይ ተሳታፊ ስለነበሩ ይሄንን አሳውቆ ከፈተናው ሂደት ራሱን ማግለል ሲገባው ያንን አላደረገም። የቅርብ ዘመዶቹ ከተወዳዳሪዎች ውስጥ የማለፍያ ነጥብ ያመጡ ቢሆንም ጉዳዩ እንደታወቀ ውድቅ እንዲሆን ተደርጓል። የሰራተኛው ጉዳይ በተመለከተ ደግሞ ከስራ እንዲታገድ ተደርጎ፤ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ክስ ተመስርቶበት የዲሲፕሊን ኮሚቴውም ከስራ እንዲሰናበት ውሳኔ ያስተላለፈበት ሲሆን በዚሁም መሰረት የስንብት ደብዳቤ ተፅፎለታል። ውሳኔው እንደተሰጠም ወደ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ክስ የመሰረተብን ሲሆን ዩኒቨርሲቲውም በሰው ሃብት ልማት ዳይሬክተር በኩል በመቅረብ መልስ ሰጥቶበታል። በኬሚስትሪ ዲፓርትመንት በተደረገው የቴክኒካል ረዳት ቅጥር ውስጥም የአንዱ ተመሳሳይ ችግር ስለነበረበት ወደ ሰኔት ቀርቦ ውይይት ተደርጎበት ቅጥሩ ውድቅ እንዲሆን ተደርጓል።

በፅዳትና በጥበቃ አከባቢ በቋሚነት የተቀጠሩት ሰራተኞች ብዛት አነስተኛ እንዲሆን የተደረገበት ምክንያት በአመታዊ ዝርዝር እቅድ በተቀመጠው መሰረት አብዛኛዎቹ በተጠቀሱት ስራዎች ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች በኮንትራት ሰራተኝነት እንዲቀጠሩ እና ስራዎቹን ወደ ውጭ ማውጣት /outsource/ አስፈላጊነትም ለማጥናት ሲባል ነው።

*በኮንትራት ከቀጠርናቸው የጥበቃ ሰራተኞች አብዛኞዎቹ ከከተማው አስተዳደር ጋር በመነጋገር አስተዳደሩ በችሎታቸውና በስነምግባራቸው የተመሰገኑት እና ትጥቅ ያላቸውን መርጠ እንዲልክልን ጥያቄ አቅርበን ተልከውልን በመስራት ላይ ይገኛሉ።*

- *የኣመቱን የትምህርት መርሃግብር ማውጣትና ማፅደቅ*

*የአመቱ የትምህርት መርሃ ግብር* /Academic Calendar/ *በዩኒቨርሲቲው ሬጂስትራር በኩል ተዘጋጅቶ ለሁሉም ትምህርት ክፍሎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጎና ተስተካክሎ ፀድቆ በተግባር ላይ ውሏል።*

- *ከዞኑና ከከተማው ኣስተዳደር ጋር በመተባበርና በመቀናጀት ኣዲስ ተማሪዎችን በደማቅ ሁኔታ መቀበል፤*

*ተማሪዎችን በደማቅ ሁኔታ የመቀበል ስራ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶዋቸው ከተሰሩት ስራዎች ወስጥ አንደኛው ሲሆን ተማሪዎችን ህዳር* 24 *እና* 25 *ወደ ግቢው እንዲገቡ በቴሌቪዥን ማስታወቅያ ተነግሮ ተማሪዎቹ ወደ ዩኒቨርሲቲው ግቢ በተጠቀሱት ቀናት ገብተዋል። ተማሪዎቹ በተጠቀሱት ቀናት በሚመጡበት ጊዜ ከአውቶቡስ መናኸርያ ጀምሮ በከተማው ነዋሪ እና በዩኒቨርሲቲው ህብረተሰብ ታጅበው ወደ ግቢው እንዲገቡ ደማቅ አቀባበል ተደርጎላቸዋል። ተማሪዎቹ የመምጣታቸው ቀናት በተቃረበበት ቀናትም በድምፅ ማጉያ ለሶስት ቀናት ያህል ስለተማሪዎቹ አመጣጥ ለከተማው ነዋሪ ገለፃ ተደርጓል። አጠቃላይ አቀባበሉን የሚያስተባብር አምስት መምህራን ያሉት ኮሚቴ /ሳሙኤል እምብዛ፤ ኢሳያስ ወልደትንሳኤ፤ ገብረዋህድ ፅጌ፤ ዮውሃንስ ከበደ እና ኣረጋዊ ገብረሚካኤል/ ተመስርቶ ሃላፊነቱን በተገቢው ተወጥቷል።*

*ተማሪዎቹ ግቢ ከመግባታቸው በፊትና በሚገቡበት ጊዜም ግቢው ለተማሪዎቹ በተቻለ መጠን ምቹ እንዲሆን ተደርጓል። የተማሪዎች ምግብ በወቅቱ እንዲዘጋጅ፤ የምግብ አዳራሽ ከነወንበሮቹ ዝግጁ እንዲሆን ማድረግ፤ የተማሪዎች መኝታ ቤቶች አልጋዎች እና ሌሎች ተጓዳኝ አገልግሎቶች ዝግጁ ማድረግ፤ በዩኒቨርሲቲው ህብረተሰብ ከፍተኛ ርብርብ እና ጥረት የተሰሩ ስራዎች ነበሩ። ወንበሮችንና አልጋዎችን ወደየቦታቸው የማጓጓዝ ስራ ሁሉም ሰራተኛ ተረባርቦ ባይሰራ ኖሮ ዝግጅቱ ፍፁም ውጤታማ ሊሆን አይችልም ነበር። በድምሩ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ከዘበኛ እስከ ሃላፊ፤ ከፅዳት እስከ መምህር ያለውን በሙሉ ሳይቆጥብ በራሱ ተነሳሽነት ሲያስፈግ በማስተባበር አልያም በቀጥታ በጉልበት በብርሃንም ይሁን በጨለማ ተረባርቦ ባይሰራ ኖሮ አቀባበሉ ስኬታማ አይሆንም ነበር። ይህ ልዩ የሆነ የአንድነት መንፈስ የተንፀባረቀበት አጋጣሚ ስለነበረ የዩኒቨርሲቲው አመሰራረት ታሪክ ቋሚ አካል ሆኖ ለዘልአለም ይኖራል።*

*ተማሪዎቹን ለመቀበል የተደረገው ሌላው ስራ የእንኳን ደህና መጣችሁ ፖስተሮች /ዲጂታል ፖስተሮች/ ተዘጋጅተው በከተማው እና በዩኒቨርሲቲ ግቢ እንዲሰቀሉ መደረጋቸው ነው።* 300 *ቲሸርቶች እና* 450 *የወረቀት ኮፍያዎችም ተሰርተው ለሰራተኞችና እንግዶች ታድለዋል። ተማሪዎቹ ተጠቃለው ከገቡ በኋላ* ***ማክሰኞ ህዳር* 26/2004 *ቀኑን ሙሉ የፈጀ ደማቅ የአቀባበል ዝግጅት ተደርጎ ዩኒቨርሲቲው በይፋ ስራውን እንደጀመረ የተበሰረበት ቀን ነበር።*** *በዚህ የመክፈቻ በኣል ላይ በከተማው ከሚገኙ ቀበሌዎች በሙሉ የተወከሉ ነዋሪዎች፤ በከተማው የሚገኙ የተለያዩ መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ተወካዮች፤ የሃይማኖት አባቶች፤ እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተው የአቀባበል ስነስርአቱን አድምቀውት ውለዋል። በአጠቃላይ ከተለያዩ ክፍሎች የተውጣጡ ከአንድ ሺ በላይ የሚሆነው የከተማው ህዝብ እና የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ በመገኘት*

ለዩኒቨርሲቲው የመጀመርያ ተማሪዎች ከፍተኛ አቀባበል አድርጎላቸዋል፡፡ በአቀባበል ዝግጅቱ የእለቱ የክብር እንግዳና የምስራቃዊ ዞን አስተዳዳሪ ክቡር አቶ ገብረመስቀል ታረቀ፤ የዓዲግራት ከተማ ከንቲባ አቶ ከሐሰ፤ የዩኒቨርሲቲው ፕረዚደንት ዶ/ር ዛይድ ነጋሽ፤ እና የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ዲን አቶ ሳሙኤል እምብዛ ንግግር ያደረጉ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ የሃይማኖት አባቶች እና የከተማው ነዋሪ ተወካዮች ተማሪዎቹን እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት ጠቃሚ መልእክቶችን አስተላልፈዋል፡፡ የተማሪዎች ተወካዮችም ለተደረገላቸው ደማቅ አቀባበልና አክብሮት ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡ የአቀባበል በአሉ የተከበረው በተማሪዎች የምግብ አዳራሽ ሲሆን ለሁለት ሺ ተሳታፊዎች የምሳ መስተንግዶ ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡ ከምሳ በኋላ ደግሞ የሰሜን እዝ የባህል ቡድን ተገኝቶ የተለያዩ አዝናኝ ዝግጅቶችን በማቅረብ ተማሪዎቹ፤ ታዳሚዎቹ እና የዩኒቨርሲቲው ህብረተሰብ ዘና እንዲል እድል አግኝቷል፡፡ የተማሪዎች አቀባበል በአል በአገራችን በየአመቱ ሕዳር 29 ከሚከበረው የብሄር ብሄረሰቦች ቀን ጋር በጥምር እንዲከበር ተደርጓል፤ የብሄር ብሄረሰቦች ቀን በተመለከተም ፅሁፍ ቀርቧል፡፡

ለተማሪዎች አቀባበል ከተደረገላቸው በኋላ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ተማሪዎችን ጨምሮ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ባጠቃላይ የዝግጅት ስልጠና መደረግ እንዳበት ከትምህርት ሚኒስቴር በተላለፈው መመርያ መሰረት ከፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በመጡ ሁለት ባለሞያዎች /አቶ እውነቱ ብላታ እና አቶ ፀጋብርሃን/ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ለሁለት ቀናት ያህል ማለትም ህዳር 30/2004 እና ታህሳስ 01/2004 በሚከተሉት ርእሶች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

1. ሕብረ ብሄራዊ ፌደራላዊ ስርአት በኢትዮጵያ
2. ልማት፤ ዲሞክራሲና የሃይማኖት አክራሪነት
3. ሰላማዊ የመማር ማስተማር ባህልን ማጎልበት
4. የአምልኮ፤ የአለባበስና የምግብ ስርአትን ለመደንገግ የወጣ መመርያ

ስልጠናው ለተማሪዎች በአንድ አዳራሽ ለሰራተኞች ደግሞ በሌላ አደራሽ የተሰጠ ሲሆን ለተጠየቁት ጥያቄዎች በቂ ማብራርያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ የስልጠናው ሪፖርት ደግሞ ለትምህርት ሚኒስቴርና ለፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ተልኳል፡፡ ስልጠናው የአመቱ ትምህርት ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ እንዲካሄድ አስተዋፅኦ ካደረጉት ተግባራት ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡

- *ለተማሪዎች ኦርየንቴሽን መስጠት፤ የትምህርት ክፍል ምደባና፤ የትምህርት ፕሮግራሞችን ማሳወቅ*

ህዳር 26 ዩኒቨርሲቲው አዲስ የተመደቡለትን ተማሪዎች ተቀብሎ በይፋ ስራውን መጀመሩ ካወጀ በኋላ ቀጥሎ የተሰራው ስራ ለተማሪዎች ኦርየንቴሽን መስጠት ነበር፡፡ ህዳር 29/2004 የኦርየንቴሽን ቀን ተሰይሞ በሚመለከታቸው ሰዎች የግማሽ ቀን ገለፃ ተደርጎላቸዋል፡፡ ኦርየንቴሽኑ የተሰጠው በየባንዱ ሲሆን የየትምህርት ክፍሉ ሃላፊዎች ተገኝተው ስለትምህርት ክፍሎቻቸው ዘርዘር ያሉ ገለፃዎችን ሰጥተዋል፡፡ ከምህንድስና ባንድ ውጭ የተመደቡት ተማሪዎች በገለፃው ወቅት ስለ እያንዳንዱ ትምህርት ክፍል እንዲያውቁ እና ምርጫ ለማድረግ ሊያግዛቸው በሚችልበት መልኩ ነበር ማብራርያዎች የተሰጡት፡፡ ገለፃውን ተከትሎ ደግሞ በረጂስትራር ተዘጋጅቶ በተሰጣቸው ፎርም ላይ የትምህርት ክፍል ምርጫቸውን በቅደም ተከተል እንዲያቀርቡ ተደርጓል፡፡

በምህንድስና ባንድ የተመደቡት ተማሪዎች ግን የትምህርት ክፍል ምርጫ የሚካሄደው በሁለተኛው ሰሚስተር መጀመርያ ስለሆነ በመጀመርያው ሰሚስተር ሁሉም አንድ ላይ ቅድመ ምህንድስና /Pre-engineering/ ላይ እንዲቆዩ ተደርገው አንድ አይነት ኮርሶችን ነው የሚወስዱት። በዚሁም መሰረት በኦርየንቴሽን እለት ትኩረት ተሰጥቶ ገለፃው የተደረገላቸው ስለ European Credit Transfer Systerm /ECTS/ ነበር። በምህንድስና ኮሌጅ የምንከተለው የትምህርት አሰጣጥ ስርአት የኢሲቲኤስ ስርአት ስለሆነ ስለስርአቱ ምንነት እና እንዴት እንደሚተገበር ማብራርያ ተሰጥቷቸዋል።

ኦርየንቴሽኑን ተከትሎ ከምህንድስና ውጭ ያሉት ተማሪዎች የትምህርት ክፍል ምርጫቸውን እንዲያመለክቱ ተደርጎ ስለነበረ የትምህርት ክፍል ምደባን የሚያከናውን በረጂስትራር የሚመራ፤ የተማሪዎች ዲን እና የትምህርት ክፍል ሃላፊዎች ያሉት /የኮሚቴው አባላት፤ ሊላይ ፈረደ፣ ሳሙኤል እምብዛ፣ ኢሳያስ ወ/ትንሳኤ፣ ደስታ ገበያ፣ እና ሃይላይ በሪሁ ናቸው/ ኮሚቴ ተቋቁሞ የድልድል ፕሮፖዛል እንዲያቀርብ ተደርጎ ፕሮፖዛሉን አቅርቧል። የተማሪዎችን ምርጫ እና የቀረበው ፕሮፖዛል መሰረት በማድረግ ሁሉም ትምህርት ክፍሎች በተገኙበት ሰፋ ያለ ውይይት ከተደረገ በኋላ ኮሚቴው ባቀረበው ፕሮፖዛል ላይ ማስተካከያ ተደርጎበት እንዲሰራ ተደርጎዋል። በተሰጠው ማስተካከያ መሰረት የተማሪዎች ምርጫን መሰረት ያደረገ ድልደላ ተደርጎ እንደገና ለውይይት የቀረበ ሲሆን ስምምነት ተደርሶበት ድልደላው ለተማሪዎች እንዲለጠፍ ተደርጓል። ተማሪዎች እንዲያውቁት ከተደረገ በኋላ የማይስማሙ ተማሪዎች ካሉ ጥያቄያቸውን በማመልከቻ እንዲያቀርቡ እድል ስለተሰጣቸው 23 የሚሆኑ ተማሪዎች አብዛኛዎቹ ወደሌላ ትምህርት ክፍል እንዲዛወሩ የተወሰኑት ደግሞ የእርስ በርስ ዝውውር እንዲፈቀድላቸው ያመለከቱ ነበሩ። የእርስ በርእ ዝውውር የጠየቁት በቀጥታ የተፈቀደላቸው ሲሆን የተመደቡበት ትምህርት ክፍል ያልተመቻቸው መሆኑን በመግለፅ ወደ ሌላ ትምህርተ ክፍል እንዲቀየሩ ካመለከቱት 17 ተማሪዎች ውስጥ ደግሞ 15 ሴቶች ስለነበሩ በዩኒቨርሲቲው አመታዊ እቅድ በተቀመጠው መሰረት ለሁሉም ሴት አመልካቾች ዝውውሩ ተፈቅዶላቸዋል። ባጠቃላይ ወደየትምህርት ክፍሉ የተደረገው አመዳደብ በተማሪዎች ምርጫ መሰረት የተደረገ ሲሆን ሴት ተማሪዎች ደግሞ በተለይ በመረጡት ትምህርት ክፍል እንዲመደቡ ተደርጓል። ዘግይተው የመጡ /ማለትም በወቅቱ ምርጫቸውን ያላመለከቱ/ ተማሪዎች ደግሞ ባሉን ክፍት ቦታዎች እንዲያመለክቱ ተደርገው ባስቀመጡት ምርጫ መሰረት ተስተናግደዋል።

- *ለመምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የዝግጅት ስልጠናዎችን መስጠት*

ዩኒቨርሲቲው እንደ መሪ ቃል /motto/ ያስቀመጠው "**ነባር ዩኒቨርሲቲዎች ከደረሱበት ደረጃ ተነስተን ወደፊት እንጓዝ**" የሚል ስለሆነ ከደረሱበት ደረጃ ለመጀመርና ለመቀጠል ደግሞ በየስራው ክፍል የተደረሰበት ደረጃ ሰራተኛው ማወቅ እንደሚገባው ታሳቢ ያደረገ ስለሆነ በርካታ የዩኒቨርሲቲው መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች ወደ ነባር ዩኒቨርሲቲዎች በመሄድ ልምድ እንዲቀስሙ ተደርጓል። ጉብኝት በማድረግ ልምድ ከመቅሰም በተጨማሪም ስልጠናዎችን ማዘጋጀት ስለሚጠይቅ ስልጠናዎችም ተሰጥተዋል።

ስልጠናን በተመለከተ በዋናነት ትኩረት የተደረገው በአካዳሚክ ሰራተኞች ነበር። ወደ ዩኒቨርሲቲው የተመደቡት መምህራን /ሁለተኛ ዲግሪ የጨረሱትም ጭምር/ የማስተማር ልምድ የሌላቸው ስለሆኑ ትምህርቱን ከመጀመራችን በፊት ስልጠና መስጠት አስፈላጊ መሆኑ በአመታዊ እቅዱ መቀመጡ የሚታወስ ነው። በዚሁም መሰረት ከመቐለ ዩኒቨርሲቲ ጋር

በመፃፃፍ በዩኒቨርሲቲው ከሚገኘው የፔዳጎጂ ጥናት ኢንስቲትዩት አሰልጣኞችን በማምጣት የአራት ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል።

በስልጠናው የተሸፈኑት ነጥቦች የሚከተሉት ነበሩ።

- Class room Management
- Assessment and Grading
- Active Teaching and Learning
- Anti-sexual Harassment and Policy Implementation

በስልጠናው የተሳተፉ መምህራን ብዛት 87 ሲሆን የተሳታፊዎች ብዛት ግምት ውስጥ በማስገባት ስልጠናው በሁለት የተለያዩ ክፍሎች የተካሄደ ሲሆን አጠቃላይ የስልጠናውን ስራ የሚያስተባብርና የሚከታተል ሶስት መምህራን ያሉት ኮሜቴ ተቋቁሞ /ተኽለብርሃን በርሁ፡ ንጉሰ ደስታ እና ጠዓመ ኣብርሃ/ ስልጠናውን የማስተባበር ስራ የሰራ ሲሆን የስልጠናው ሪፖርትም አዘጋጅቶ አቅርቧል። የስልጠናው ጠቀሜታና አካሄድ በተመለከተም የትምህርት ክፍሎች ሃላፊዎች በተገኙበት የግምገማ ውይይት ተደርጎ የጊዜ ማጠር የነበረ ቢሆንም ስልጠናው በጥሩ ሁኔታ እንደተካሄደ እና ጥሩ ጠቀሜታ እንደተገኘበት ተገምግሟል። ተመሳሳይ የኢንዳክሽን ስልጠናዎች በየትምህርት አመቱ መጀመርያ በተለይ ለአዳዲስ መምህራን የሚካሄዱ ይሆናሉ።

ከተጠቀሰው ስልጠና በተጨማሪ በተለይ በምህንድስና ኮሌጅ ላሉት መምህራን ስለ European Credit Transfer System (ECTS) ህዳር 11/2004 የግማሽ ቀን ስልጠና ተሰጥቷል። ስልጠናውን የሰጡልን ዶ/ር ገብረመስቀል ካሕሳይ /የመቐለ ዩኒቨርሲቲ ኢንጂነሪንግ ኮሌጅ ዲን የነበሩና አሁን በመቐለ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በመስራት ላይ የሚገኙት/ ሲሆኑ ስልጠናው በጣም ጠቃሚ ነበር። ስልጠናውን ተከትሎ በምህንድስና ስር ባሉት ትምህርት ክፍሎች የትምህርት አሰጣጥ እና አመዛዘን ስርአቱን በኢሲቲኤስ መሰረት እንዲካሄድ ተደርጓል።

የድጋፍ ሰጪ ስራተኞች ስልጠናን በተመለከተ በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፤ በግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት፤ በትምህርተ ሚኒስቴር፤ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እንዲሁም እና በሌሎችም በኩል በዋናነት ለፋይናንስ አስተዳደር፤ ለግዥና ንብረት አስተዳድር፤ እና ለውስጥ ኦዲት ሰራተኞች በርከት ያሉ ስልጠናዎች የተሰጡ ሲሆን በዩኒቨርሲቲው በአብዛኛው የተሰራው ስራ ወደ ነባር ዩኒቨርሲቲዎች እና የሚመለከታቸው ሌሎች ክፍሎች በመሄድ ልምድ የመቅሰም አካሄድ ነበር። በዚሁም መሰረት ትምህርተ ከመጀመሩ በፊት በድምሩ 63 የተማሪዎች ዲን ሰራተኞች ወደ መቐለ ዩኒቨርሲቲ እና ወደ አክሱም ዩኒቨርሲቲ ለአንድ ሳምንት ቆይተው ልምድ ቀስመው ተመልሰዋል። ከነዚህ ውስጥ 32 ወደ መቐለ ዩኒቨርሲቲ የሄዱ ሲሆን 31 ደግሞ አክሱም ዩኒቨርሲቲ የሄዱ ናቸው። ሰራተኞቹ በአካል ሄደው የሚሰራውን ስራ እንዲያዩና ከየተመሳሳይ ክፍሎች ጋር እንዲወያዩ የተደረገው ወደ ዩኒቨርሲቲያችን የተመደቡት ተማሪዎች ከመምጣታቸው ቀደም ብሎ ስለነበር በጣም ጠቃሚ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል። ከዚሁም በተጨማሪ የሰው ሃብት ልማት ማእከል ሰራተኞች፤ የቤተ መፃህፍት ሰራተኞች፤ የመሰረታዊ አገልግሎት ሰራተኞች እና የንብረት አስተዳደር ሰራተኞች መቐለ ዩኒቨርሲቲ እና አክሱም ዩኒቨርሲቲ ድረስ በመሄድ ውይይቶችን በማካሄድ ጠቃሚ ልምዶች እንዲያገኙ ተደርገዋል። እነዚህ ስልጠናዎችና የልምድ ልውውጦች ለስራችን ጥሩ ድጋፍ ያደረጉልን ነበሩ።

በተለይ የውስጥ ኦዲት ክፍል ሰራተኞች በተመለከተ ቅጥር ከተደረገ በኋላም የፅ/ቤቱ ሃላፊ እና ኤክስፐርት ወደ አዲስ አበባ በመሄድ ከትምህርት ሚኒስቴር፤ ከፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፤ እና ከግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ስልጠናዎች የተቀበሉና የልምድ ልውውጦች ያካሄዱ ሲሆን የአሰራር ምንዋሎችም አምጥተዋል። ከዚሁም ሌላ ሁለት የፋይናንስ አስተዳደር እና አንድ የእቅድና ተቋማዊ ማሻሻያ ፅ/ቤት ሰራተኛ ሰለ ፕሮግራም ባጀት ስልጠና ለመውሰድ አዲስ አበባ ተልከው ስልጠናውን ተከታትለዋል። ግዥና ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ ደግሞ አምስት የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞቻችን /ሶስት ከግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ሁለት ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት አንድ ደግሞ ከውስጥ ኦዲት/ ተመርጠው በፌደራል ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በሚሰጠው ስልጠና ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል።

ለመምህራን ስልጠና መሰጠቱ ከላይ የተጠቀሰ ሲሆን ከስልጠናው በኋላ እና ተማሪዎች መጥተው ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የካሪከለም እና የማስተማርያ ማቴርያሎች ዝግጅት መደረግ ስለሚኖርበት ከሁሉም የትምህርት ክፍሎች የተውጣጡ መምህራን ወደ በርካታ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሄዱ በማድረግ የተዘጋጁ ካሪከለሞችና የመማርያ ማቴርያሎች /መፃህፍት፤ ሞዱሎች። የተጠረዙ ማቴርያሎች፤ ወዘተ/ እንዲያመጡ ተደርጓል። ይህ ስራ በአመታዊ እቅዱ የተቀመጠና በከፍተኛ ደረጃ ትኩረት የተሰጠበት ስራ ስለነበረ መምህራን ወደ ዩኒቨርሲቲዎች ከመላካቸው በፊት ሁሉም ትምህርት ክፍል ሃላፊዎች እና የዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት በተገኙበት ውይይት እና መግባባት እንዲደረስበት ተደርጓል። የመምህራን ጉዞ እንዴት መዘጋጀትና መመራት እንዳለበት፤ የቲም መሪዎች አመዳደብ፤ የሚሰሩት ስራዎች ዝርዝር፤ ለሚያመጡዋቸው ማቴርያሎች የሚያስፈልግ ገንዘብ፤ እና ለስልክ ወጪ በተመለከቱ ጉዳዮች ዝግጅት ተደርጎበት የተሰራ ስራ ነበር።

በዚሁም መሰረት ትምህርት ከመጀመሩ በፊት 49 መምህራን ወደ ተለያዩ ነባር ዩኒቨርሲቲዎች የሄዱ ሲሆን ትምህርት ከተጀመረ በኋላም በዋናነት በሚቀጥለው አመት እንጀምራቸዋለን ብለን ባሰብንባቸው የትምህርት አይነቶች መሰረት ባደረገ መልኩ በርከት ያሉ ቆየት ብለው የተመደቡልን መምህራን ወደተላያዩ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሄዱ ተደርጓል። ቆየት ብለው ወደ ተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የተላኩት የጂኦግራፊ፤ የግብርና፤ የምህንድስና መምህራን ይገኙበታል። በድምሩ 62 መምህራን ወደ 8 ነባር ዩኒቨርሲቲዎች ሄደው አስፈላጊ ቆይታ በማድረግ የካሪከለም እና የማቴርያሎች ዝግጅቶች ተደርገዋል። ወደተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የተደረገው ጉዞ በየትምህርት ክፍሉ እና ጉብኝት በተደረባቸው ዩኒቨርሲቲዎች ሲጠቃለል የሚከተለውን ይመስላል።

ሰንጠረዥ 8. ወደተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የተላኩ መምህራን

| ተ.ቁ. | ትምህርት ክፍል/ትምህርት አይነት | የመምህራን ብዛት | ጉብኝት የተደረገባቸው ዩኒቨርሲቲዎች | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ፊዚክስ | 5 | መቐለ፤ አዲስ አበባ፤ አክሱም፤ ጎንደር | |
| 2 | ኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ | 7 | መቐለ፤ አዲስ አበባ፤ አክሱም፤ ጎንደር፤ አዳማ | |
| 3 | ሂሳብ | 6 | መቐለ፤ አዲስ አበባ፤ አዋሳ | |
| 4 | ሜካኒካል ምህንድስና | 3 | መቐለ፤ ባህር ዳር፤ አዳማ | |
| 5 | እንግሊዝኛ | 6 | መቐለ፤ አዲስ አበባ፤ አክሱም፤ ጎንደር | |
| 6 | ኬሚስትሪ | 3 | መቐለ፤ ባህር ዳር | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 7 | ባዮሎጂ | 6 | መቐለ፤ አዲስ አበባ፤ ባህርዳር | |
| 8 | ማኔጅመንት | 3 | መቐለ፤ አዲስ አበባ፤ አክሱም፤ ጎንደር | |
| 9 | ኢኮኖሚክስ | 6 | መቐለ፤ አዲስ አበባ፤ ባህርዳር | |
| 10 | ሲቪክስና ኤቲክስ | 4 | መቐለ፤ ባህርዳር | |
| 11 | አካውንቲንግ | 1 | መቐለ | |
| 12 | ባዮቴክኖሎጂ | 2 | ጎንደር | ትምህርት ከተጀመረ በኋላ |
| 13 | ጂኦግራፊ | 2 | ባህርዳር | ትምህርት ከተጀመረ በኋላ |
| 14 | ግብርና | 2 | ሀረማያ | ትምህርት ከተጀመረ በኋላ |
| 15 | ኬሚካል ኢንጂነሪንግ | 4 | መቐለ፤ አዲስአበባ፤ አዳማ፤ ባህርዳር | ትምህርት ከተጀመረ በኋላ |
| 16 | ሲቪል ምህንድስና | 2 | አዲስ አበባ | ትምህርት ከተጀመረ በኋላ |
| ድምር | | 62 | 8 | |

ከላይ በሰንጠረዡ እንደተመለከተው በርከት ያሉ መምህራን ወደ ተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ሄደው በየዩኒቨርሲቲዎቹ የሚጠቀሙባቸውን የማስተማርያ ማቴርያሎችን እና መፃህፍትን በአብዛኛው በቅጂ መልክ በተጨማሪም በግዥ እና በስጦታ መልክ ለማሰባሰብ ችለናል። ይህ ስራ ውጤታማ ነበር ተብሎ ሊገለፅ ይችላል። ትምህርት በአግባቡ ለማስጀመር እና ለማካሄድ የሚያስችሉን የካሪክለም ዝግጅት እና ማቴርያሎችን ማሰባሰብ መቻሉን ሁሉም ትምህርት ክፍሎች በተገኙበትና የጉዞው ውጤታማነት አስመልክቶ በተደረገው ግምገማ ማረጋገጥ ችለናል። የተሰበሰቡት ማቴርያሎች ወደ ንብረት ክፍል በአግባቡ ገቢ እንዲደረጉ የተደረጉ ሲሆን ወጪ መደረግ ያለባቸው ደግሞ በአግባቡ ወጪ እየተደረጉ ጥቅም ላይ በመዋል ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

- *የአካዳሚክና አስተዳደር አካላትን በየደረጃው ማዋቀር*

የአስተዳደር አካላት በተመለከተ በፀደቀው መዋቅር መሰረት የተዋቀሩ ሲሆን የሰው ሃብት ልማት፣ የፋይናንስ አስተዳደር፣ የግዥና ንብረት አስተዳደር፣ እና የመሰረታዊ አገልግሎት ማእከል ዳይሬክተሮች ተቀጥረዋል። ከዚሁም በተጨማሪ የዩኒቨርሲቲው ረጂስትራርና የተማሪዎች ዲን ከመምህራን ስለተመደቡ ከረጂስትራርና ከተማሪዎች ዲን /ምግብ ቤት፣ ተማሪዎች መኖርያና ተማሪዎች ህክምና/ ጋር የተያያዙ ስራዎች የሚሰሩ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በነዚህ ስር እንዲመደቡ ተደርጓል። ይሁን እንጂ አንዳንድ ቦታዎች /ለምሳሌ ላይብረሪ/ ገና ሃላፊ ያልተቀጠረላቸው ስለሆን ከተቀጠሩት ውስጥ አስተባባሪ ተመድቦ በመስራት ላይ ይገኛሉ።

የሴቶች ጉዳይ ፅ/ቤት ሃላፊን በተመለከተ በጋዜጣ ወጥቶ ያመለከቱት አመልካቾች ሁሉም ወንዶች በመሆናቸው ህዳር 15/2004 በተደረገው የቦርድ ስብሰባ ጉዳዩ ታይቶ ቅጥሩ እንዲቆይና ከዞኑ አስተዳደር ጋር በመነጋገር ለቦታው ሴት ተወዳዳሪዎች ታይተው የሚቀጠሩበት ሁኔታ እንዲታይ ተወስኖ የነበረ ቢሆንም ከዞኑ አስተዳደር ጋር በተደረገው መግባባት ዩኒቨርሲቲው ካሉት ሴት አስተማሪዎች በጊዚያዊነት ሃላፊ እንዲመድብ ስምምነት

ስለተደረሰ የዩኒቨርሲቲው መምህር የሆኑት ወ/ት ሰላማዊት ተኽሉ የፅ/ቤቱ ጊዜያዊ ሃላፊ ሆነው ተመድበው ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛሉ።

የአካዳሚክ ክንፉን በተመለከተ ደግሞ ቀደም ብሎ የትምህርተ ክፍል እና የኮሌጅ እና ሌሎች ተመሳሳይ /የተማሪዎች ዲን እና ሬጂስትራር/ ሃላፊዎች በተጠባባቂነት ተመድበው የነበረ ሲሆን የመምህራን ተሳትፎ እና የዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት ይሁንታ በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲሰራ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት የኮሌጅ ዲኖችና የትምህርተ ክፍል ሃላፊዎች እንዲመደቡ ተደርጓል። በዚሁም መሰረት የትምህርተ ክፍል ሃላፊዎች በየትምህርተ ክፍሉ የሚገኙ መምህራን በምርጫ ሶስት እጩዎችን እንዲያቀርቡ ተደርጎ ከቀረቡት ውስጥ በዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት እየታየ እንዲመደቡ ተደርጓል። የኮሌጅ ዲኖች በተመለከተም ፍላጎት ያላቸው በማስታወቅያ እንዲያመለክቱ ተደርጎ ቀደም ብለው በወጣ የመምረጫ መስፈርት መሰረት ለቃለ መጠይቅ እንዲቀርቡ ተደርገው ሃላፊዎቹ እንዲመደቡ ተደርጓል።

የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕረዚደንት ደግሞ ህዳር 15/2004 በተደረገው የቦርድ ስብሰባ በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ዶ/ር አለም መብራህቱ ፈቃደኛ ሆነው ስለተገኙ የሹመት ደብዳቤ ተፅፎላቸው ስራቸውን እያከናነኑ ነው። የአስተዳደርና ልማት /ድጋፍ ሰጪ/ ምክትል ፕረዚደንት ደግሞ ቀደም ብለው አክሱም ዩኒቨርሲቲ ሲሰሩ የነበሩት አቶ መኮንን አረጋይ ከሚያዝያ 01/2004 ጀምሮ ተመድበው ስራ ጀምረዋል።

ዩኒቨርሲቲው በሚቀጥለው አመት 3260 ያህል ተማሪዎችን ለመቀበል ያቀደ ሲሆን ልንቀበላቸው ያሰብናቸው የተማሪዎች ብዛት በየባንዱና በየትምህርት ክፍሉ ለትመህርት ሚኒስቴር አሳውቀናል። አሁን ካሉት አራት ኮሌጆች በተጨማሪ ሁለት ኮሌጆችን /ማለትም የግብርና እና የጤና ሳይንስ/ ለመክፈት በእቅድ ይዘናል። ዩኒቨርሲቲው እያሰበ ካለው የመስፋፋት ስራ ጋር ተያይዞ ሲታይ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ፀድቆ አሁን እየተጠቀምንበት ያለነው መዋቅር /በሰራተኞች አይነትና ብዛት ሲታይ/ በቂ ሆኖ አልተገኘም። ከዚሁም ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ዩኒቨርሲቲው በቀጣይነት እያደገ የሚሄድ መሆኑ ነው። ስለዚህ ይሄንን እድገት ሊሸከም የሚችል መዋቅር ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በዚሁም መሰረት አዲስ የዩኒቨርሲቲው መዋቅር የሚያዘጋጅ ኮሚቴ ተቋቁሞ ከነባር ዩኒቨርሲቲዎች ልምድ እንዲወስድ ተደርጎ መዋቅሩን ያዘጋጀ ሲሆን በዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ካውንስል ታይቶ ማስተካከያዎች ከተደረጉለት በኋላ ለቦርድ እንዲቀርብ ተዘጋጅቷል። በቦርድ ከታየ በኋላ ወደ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ተልኮ እንደፀደቀ የሚሰራበት ይሆናል።

- *የተጠናከረ የማባዣ ክፍል በማደራጀት ከነባር ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙትን መፃህፍትና የማስተማርያ ማቴርያሎች ማዘጋጀትና ማቅረብ*

የማስተማርያ ማቴርያሎችን ከነባር ዩኒቨርሲቲዎች የማሰባሰብ ስራ በአጥጋቢ ሁኔታ መሰራቱ ቀደም ብሎ ተገልጿል። የተሰበሰቡት ማቴርያሎች ግን ባሉበት ሁኔታ ሳይባዙ ለመምህራን እንጂ ለተማሪዎች ሊዳረሱ አይችሉም። ስለዚህ ማቴርያሎችን አባዝቶ በላይብረሪ የማስቀመጡ ስራ በሰፊው መሰራት ያለበት ጉዳይ ነው። የተመረጡ ማቴርያሎችን ለማባዛት ያስችለን ዘንድ ደግሞ የማባዣ ማሽኖች /ሪዞዎች/ የመግዛቱ አስፈላጊነት በአመታዊ ፕላኑ በተቀመጠው መሰረት ግልፅ ጨረታ ላይ እንዲወጣ ተደርጎ ከቀረቡት ተወዳዳሪዎች ውስጥ አሸናፊ ተለይቶ አራት የማባዣ ማሽኖች /Rizo EZ 370/ ተገዝተው የማባዛት ስራው እየተሰራ ይገኛል። ከማባዛት ስራው ጋር ተያይዞ ግን ለማባዣ ሰራተኝነት የፀደቀ ቦታ ስላልነበረን ለላይብረሪ ከተቀጠሩት ውስጥ ሁለት ሰራተኞችን መድበን የማባዛቱን ስራ

በመስራት ላይ ይገኛሉ። በአዲሱ መዋቅር ግን የራሱ አደረጃጀትና የሰው ሃይል የተመደበለት ስለሆነ በቅጥር ወይም በእድገት የሚሞላ ይሆናል።

መፃህፍትና የማስተማርያ ማቴርያሎች ከነባር ዩኒቨርሲቲዎች ከማሰባሰብ በተጨማሪም ከሌሎች ምንጮችም ለማግኘት ችለናል። በዚሁም መሰረት በዋነኛነት ሊጠቀስ የሚችለው ከኤንጂነሪንግ ካፓሲቲ ቢልዲንግ ፕሮግራም /ECBP/ የዩኒቨርሲቲው ቦርድ አባል በሆኑት ዶ/ር መብራህቱ አጋዥነት ማቴርያሎቹ በሶፍት ኮፒ እንዲያበረክቱልን ባቀረብነው ጥያቄ መሰረት በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ በተለይ ለምህንድስና እና ለተፈጥሮ ሳይንስ የሚሆኑ መፃህፍትና የማስተማርያ ማቴርያሎች /በቪድዩ የተደገፉ/ ተበርክተውልናል። ከግለሰቦችም በሶፍት ኮፒ ያሰባሰብናቸው መፃህፍት በርካታ ናቸው። ትምህርት ሚኒስቴር ቀደም ብሎ አውጥቶት በነበረው ጨረታ መሰረት ካሸነፉት ውስጥ የተወሰኑ የምህንድስና መፃህፍት ተረክበናል /ከ 1000 በላይ/። ሌሎችም በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን።

ትምህርት ሚኒስቴር በስጦታ ካገኛቸው ውስጥም የላከልን በርከት ያሉ መፃህፍትም በስጦታ አግኝተናል። እስካሁን ከትምህርት ሚኒስቴር ከሁለት ሺ በላይ የሚሆኑ መፃህፍት ተልከውልናል። በአሜሪካ ከምትኖር የአከባቢው ነዋሪ ደግሞ 23 የህክምና መፃህፍት አግኝተናል። ዓዲግራት ከተማ ከሚገኙት የአግአዚ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና የፖሊቴክኒክ ኮሌጅ በጣም ተፈላጊ የሆኑ 160 ያህል የኬሚስትሪ 32 የባዮሎጂ መፃህፍት ሰጥተውናል። የመፃህፍት ድጋፍ ላደረጉልን ሁሉ ምስጋና ማቅረብ ተገቢ ስለሆነ ምስጋናችንን እናቀርባለን። የታወቁ የአገራችን ጋዜጦችም /አዲስ ዘመን፤ ሄራልድ፤ ፎርቹን፤ ሪፖርተር/ በገባነው ውል መሰረት እየመጡልን ናቸው።

በራሳችን የመፃህፍት ግዥም አካሂደናል። ከዚህ ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሰው በባጀት አመቱ መጨረሻ ላይ ለምርምር ተመድቦ ከነበረው እና ጥቅም ላይ ካልዋለው ውስጥ የ170000.00 ብር መፃህፍት በለቀማ እንዲገዛ ማድረጋችን ነው። የለቀማ ግዥው ለማካሄድ ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ጋር ተፃፅፈን በተፈቀደልን መሰረት ነው ግዥው የተካሄደው። ባጠቃላይ ላይብረሪያችን ገና በቂ መፃህፍት የሌሉት ቢሆንም የማቴርያሎች ክምችቱ እየጨመረ በመሄድ ላይ ነው።

ከላይ በዝርዝር የቀረቡት የመጀመርያውን ግብ የተመለከተ ሲሆኑ ሌሎች ግቦችን በተመለከተ ደግሞ ያለው የትግበራ ሪፖርት በሚከተለው ሰንጠረዥ ተጠቃሎ ቀርቧል።

## 3. የ2004 የባጀት አመት የአመቱ የስራ አፈፃፀም ሰንጠረዥ

| ግቦች | ሊሰሩ የታቀዱ ስራዎች | የአመቱ እቅዱ ኣፈፃፀም በመቶኛ (እስከነማብራርያው) | እቅዱ እንዳይፈፀም ያጋጠሙ ችግሮች ወይም ሁኔታዎች | የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች |
|---|---|---|---|---|
| ግብ 2. ተቋማዊ መልካም ኣስተዳደርን ማስፈንና ማስጠበቅ | 2.1 የዩኒቨርሲቲው ኣመታዊ እቅድ ማዘጋጀትና በኣመታዊ ዝርዝር እቅዱ መወያየትና መግባባት መፍጠር | አመታዊ ዝርዝር እቅዱ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ሐምሌ 2003 ተዘጋጅቶ ከመምህራንና ሰራተኞች ጋር መስከረም 5/2004 የግማሽ ቀን ውይይት ተደርጎበታል። ስራው ሙሉ ለሙሉ ተስርቷል /100%/ | | |
| | 2.2. የዩኒቨርሲውን እቅድ መሰረት በማድረገ የተለያዩ የዩኒቨርሲቲው ክፍሎች የየራሳቸውን እቅድ እንዲያወጡና ከክፍሎቻቸው ሰራተኞች ጋር እንዲወያዩባቸው ማድረግ | የተለያዩ የዩኒቨስቲው ክፍሎች ከሰራተኞች ጋር በመወያየት የየክፍላቸውን እቅድ አውጥተው ህዳር 16/2004 በተደረገው ጠቅላላ የሰራተኞች ስብሰባ አንድ በአንድ አቅርበው ውይይት ተደርጎበታል። አፈፃፀሙ 100% ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል | | |
| | 2.3. የግዢና የንብረት ኣስተዳደር ስራዎች በመንግስት በመጡት መመርያዎችና ማንዋሎች መሰረት በተቀላጠፈና ከሙስና በፀዳ መልኩ ማከናወን። የ2005 ባጀት በወቅቱ በማዘጋጀት በሚመለከታቸው ክፍሎች ፀድቆ እንዲላከ ማድረግ። | በባጀት አመቱ በርከት ያሉ የፕሮፎርማ፤ የቀጥታ ፤ እና የውሱን ጨረታዎ ግዥዎች እና ሁለት ግልፅ ጨረታ ደግሞ በጋዜጣ ወጥተው ግዥዎች ተካሂደዋል። በግልፅ ጨረታ ከተገዙት ማቴርያሎች ውስጥ 150 ላፕቶፕ ኮምፕዩተሮች /ለሁሉም መምህራን አንድ አንድ ኮምፕዩተር እንዲደርሳቸው ተደርጓል/፤ 20 ላፕቶፕ ኮምፕዩተሮች፤ 80 የመፃህፍት መደርደርያዎች /ሽልፎች/፤ ቴሌቪዥኖች፤ አራት የማባዣ ማሽኖች፤ አራት የሻይ ማፍያ ማሽኖች፤ በርካታ ወንበሮችና ጠረጴዛዎች፤ የጤፍ የሽሮና የበርበሬ አቅርቦት፤ ሶፋዎች ይገኙበታል። የሁለተኛው ግልፅ ጨረታ አሸናፊዎች ተለይተው ውል ታስሮ አንዳንድ እቃዎችን የተረከብን ሲሆን /ጠረጴዛና ወንበር፤ ሸልፍ/ በርከት ያሉ በወቅቱ ያላቀረቡ አሸናፊዎች አጋጥመዋል። ከነዚህም በዋናነት የሚጠቀሱት 120 ዴስክቶፕ ኮምፕዩተሮች፤ ሳውንድ ሲስተም፤ የኢንጂነሪንግ እቃዎች ይጠቀሳሉ። አሸናፊዎች በሙሉ ያቀርቡልናል በሚል እሳቤ ከ3 ሚልዮን በላይ ተጨማሪ ባጀት ጠይቀን ያስፈቀድንም ቢሆንም እቃዎቹን ማቅረበ ባለመቻላቸው ምክንያት ገንዘቡን ልንጠቀምበት አልቻልንም። ለ2005 የባጀት ጥያቄ የማዘጋጀቱ ስራ በጥሩ ሁኔታ የፕሮግራም ባጀት አሰራርን መሰረት ባደረገ መልኩ የተሰራ ሲሆን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በጊዜው | በአንደኛው ግልፅ ጨረታ ወቅት በተለይ የኤ 4 ወረቀት አሸናፊ ያሸነፈውን እቃ ሊያቀርብ አልቻለም። በሁለተኛው ጨረታ ደግሞ በርከት ያሉ አቅራቢዎች ያሸነፉትን እቃ በወቅቱ ሊያቀርቡ አልቻሉም። | በስፔሲፊኬሽኑ መሰረት ማቅረብ ያልቻሉት አሸናፊዎች ያስያዙት ገንዘብ ገቢ እንዲሆን ተደርጓል። |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ተልኳል፤ ፀድቆ የሚላክልንን የ2005 ባጀት በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን። አፈፃፀሙ 100% ነበር | | |
| | 2.4.የኢንተርኔት አገልግሎት በሲዲኤምኤ እና ኢቪዶ አመካኝነት ከትምህርተ ክፍል ሃላፊ ጀምሮ ለሁሉም ክፍሎች ማዳረስ። | የሲዲኤምኤ ጨረታ ወጥቶ አሸናፊው ተለይቶ ግዥው ፈተፅሟል። የሲዲኤምኤ ካርድ ደግሞ ተገዝቶ ለትምህርት ክፍል ሃላፊዎች ቅድሚያ በመስጠት እንዲዳረስ ተደርጎ በየወሩ ካርድ ተመድቦላቸው ኢንተርኔት በመጠቀም ላይ ይገኛሉ። ለመላው መምህራን ደግሞ በኢቪዶ በሚሰራ ኔትወርክ እንዲዳረስ በታቀደው መሰረት ዝግጅት ተደርጎበት የነበረ ቢሆንም ሰርቪሱን ለመስጠት በሚሞከርበት ጊዜ ግን በአከባቢው ያለው የኢንተርኔት ሽፋን በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ አገልግሎት ሳይሰጥ ቆይቶ ነበረ። ሆኖም ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ባደረግነው ተደጋጋሚ ግንኙነት በአንድ በኩል ለዘላቂ መፍትሄ የፋይበር ኦፕቲክ መስመር ዝርጋታ ለመጀመር በዝግጅት ላይ ስንሆን በሌላ በኩል ደግሞ በግቢው አንድ ቦታ ላይ ደህና የሆነ የኢንተርኔት ግንኙነት ያለበት ክፍል ተገኝቶ እዛው ክፍል ውስጥ ሰርቨሩን በማስቀመጥ እና የኮምፕዩተር ላቦራቶሪም ሰርቨሩ ወዳለበት አቅራቢያ በማዘዋወረ የኢንተርኔት አገልግሎት በኢቪዶ በኩል ለመምህራንና ሰራተኞች በመሰጠት ላይ ይገኛል። የዳታ ሰንተር ህንፃ ተለይቶ የሚገጠሙ አቃዎች መገጠም ጀምረዋል ሆኖም የፋይበር ኦፕቲክ መስመር ዝርጋታ አልተሰራም። /አፈፃፀሙ 90 ፐርሰንት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል/ | በአከባቢው ያለው የኢንተርኔት ሽፋን ዝቅተኛ በመሆኑ በኢቪዶ የኢንተርኔት አገልግሎት ለመስጠት አስቸግሮ ነበር። | ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ተደጋጋሚ ግንኙነቶችን በማድረግ ችግሩ በከፊልም ቢሆን ሊደረግ ችሏል። ለዘላቂ መፍትሄነት ደግሞ የፋይበር ኦፕቲክ መስመር ዝርጋታ ወደ ግቢው ለማድረገ የዋጋ ግምት ወጥቶለት በራሳችን ገንዘብ ለማስገባት አስበን የነበረ ቢሆንም በመንግስት ለሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የተያዘ ፕሮጀክት መኖሩ ስላወቅን በዛ በኩል እስኪዘረጋልን በመጠባበቅ ላይ ነን። |
| | 2.5. ጊዜያዊ ዌብሳይት ማዘጋጀትና ለኣገልግሎች ማቅረብ | ዩኒቨርሲቲው ዌብ ሳይት ያዘጋጀ ሲሆን ጠቃሚ መረጃዎች /የጨረታ ዶኩመንቶች፡ የዩኒቨርሲቲው እንቅስቃሴዎች፡ እና የተመደቡ ተማሪዎች ዝርዝር/ በዌብሳይቱ እንዲቀመጡ ተደርጓል። ተማሪዎች ከመግባታቸው በፊት የተመደቡበት መኝታ ክፍልና አልጋ ቁጥት በዌብሳይት እንዲያውቁት ተደርጓል። የዩኒቨርሲቲው የዌብሳይት አድራሻ www.adu.edu.et ነው። ዌስሳይቱን በሺዎች የሚቆጠሩ ጎብኝዎችም እንደጎበኙት ለማወቅ ተችሏል። አፈፃፀሙ 100% ነው። | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 2.6. ልዩ ጠቀሜታ ያላቸው ሶፍትዌሮች /ለምሳሌ የረጂስትራር፤ የፋይናንስ ወዘተ/ ከትምህርት ሚኒስቴርና ከአዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመመካከር እንዲሰሩ /በጋራ ለሁላችንም ሊያገለግል በሚችል መልኩ/ ጥረት ማድረግ | 150 ዴስክቶፕ ኮምፕዩተሮች ተገዝተው ፍተሃዊ በሆነ መንገድ ለሁሉም መምህራን፤ እና ለሁሉም ቢሮዎች ስለተከፋፈሉ ስራዎችን በኮምፕዩተር በማሳለጥ ላይ እንገኛለን። ሆኖም የምንጠቀምባቸው ሶፍትዌሮች በተለይ ለዩኒቨርሲቲው የተዘጋጁ ሳይሆኑ አጠቃላይ ጠቀሜታ ያላቸውን ሶፍትዌሮች ነው። ከሌሎች አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በተለይ የተማሪዎች ዶኩመንቶች አያያዝ፤ የሰውሃብትና ንብረት አያያዝ ወዘተ ሊያገለግል የሚችል የሶፍትዌር ዝግጅት በተመለከተ ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች በተገኙበት ሃሳቡን ያቀረብን ሲሆን ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በተለይ ለተማሪዎች ማህደር አያያዝ የሚያገለግል ሶፍትዌር ያዘጋጀ መሆኑ በገለፀልን መሰረት አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ሶፍትዌሩን ባለሞያዎቻቸው ባህርዳር ድረስ ልከው እንዲያዩት ያደረጉ ሲሆን ከአዲሶቹ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመሆን ያንን ሶፍትዌር ለማግኘትና ለመጠቀም እየተሰራበት ይገኛል። የፋይናንስ አሰራሩን አውቶሜት ለማድረግ ከፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት በተላኩት ባለሞያዎች አይቤክስ የተባለው የፋይናንስ ሶፍትዌር የተጫነልን ቢሆንም ገና ጥቅም ላይ ግን አልዋለም። | በአይቤክስ የሰለጠነ ባለሞያ አለመኖር | ለ2005 ባጀት በአይቤክስ እንዲሰራ ዝግጅቶች እየተደረጉ ነው |
| | 2.7. *መመርያዎችን /የሰኔት ለጂስሌሽን፤ የቅጥርና ስኮላርሺፕ ማንዋሎች፤ የምርምርና ህብረተሰብ ኣገልግሎች መመርያ፤ የጥራትና ተገቢነት ማንዋሎች/ ለማውጣትና ለማፅደቅ መሰራተዊ ስራዎችን ማከናወን ።* | *መመርያዎችን ከነባር ዩኒቨርሲቲዎች የማሰባሰብ ስራ የተሰራ ሲሆን አንዳንድ መመርያዎች /ለምሳሌ የተከታታይ ትምህርት/ ተሰርተው ተተግብረዋል። ሌጂስሌሽን በተመለከተ ደግሞ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተዘጋጀው* Harmonized Academic Policy of Ethiopian Public Higher Education Institutions *የፀደቀ ቢሆን የመጨረሻው ጥራዝ እንደደረሰን ተግባራዊ የምናደርገው ይሆናል።* | | |
| | 2.8. በየሩብ ኣመቱ ሪፖርቶችን ማዘጋጀትና በሪፖርቶቹ ውይይቶችን ማካሄድ | የአንደኛው ሩብ አመት ሪፖርት ተዘጋጅቶ በቦርድ ውይይት ተደርጎበት ከፀደቀ በኋላ ለዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ሃላፊዎች /እስከ ትምህርት ክፍል ድረስ/ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል። የአመቱ አቅድና የአንደኛው አመት ሪፖርት ለትምህርት ሚኒስቴር እና በተወካዮች ሚኒስቴር ለሰው ሃብት ልማት ቋሚ ኮሚቴ ተልኳል። ቋሚ ኮሚቴውም በተላከለት የዩኒቨርሲቲ እቅድና የሩብ አመት ሪፖርት ያለውን ግብረ መልስ ልኮልናል። የስድስት ወር ሪፖርት ደግሞ በሁሉም የዩኒቨርሲቲው ክፍሎች ተዘጋጅቶ ጥር 5/2004 በተደረገው ጠቅላላ የሰራተኞች ስብሰባ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል። የስድስት ወር ሪፖርቱ ለቦርድ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበት ፀድቋል። የዘጠኝ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወራት ሪፖርትም በተመሳሳይ ተዘጋጅቶ ለቦርድ ቀርቦ ፀድቋል። የአመቱ ሪፖርት ደግሞ ተዘጋጅቶ ሰኔ 30/2004 በተደረገው የጠቅላላ ሰራተኞች የስራ አፈፃፀም ግምገማ ውይይት ተደርጎበታል። /አፈፃፀሙ 100% ነው/ | | |
| | 2.9. የዩኒቨርሲቲው ኣስተዳደር ካውንስል በየሳምንቱ ኣንድ ጊዜ እየተገናኘ ኣፈፃፀሞችንና ሂደቶችን መከታተል | ምክትል ፕረዚደንቶች ከተሟሉበት ጊዜ ጀምሮ የአስተዳደር ካውንሉ በሳምንት አንድ ጊዜ በመገናኘት የተለያዩ ውሳኔዎችን አሳልፏል ስራዎችንም ገምግሟል። ቀደም ብሎ ምክትል ፕረዚደንቶች ባልተሟሉበት ጊዜ ደግሞ ሁሉም ዳይሬክተሮችና የትምህርት ክፍሎች የሚገኙባቸው ተደጋጋሚ ግንኙነቶችና በማድረግ የመከታተል ስራዎች ተሰርተዋል /100%/ | | |
| | 2.10. የዩኒቨርሲቲው ሰኔት በወር ኣንድ ጊዜ እየተገናኘ ክትትሎችን ማድረግና ውሳኔዎችን ማሳለፍ | ሰኔቱ ተዋቅሮ ስራውን በማከናወን ላይ ይገኛል። በፕላኑ በወር አንድ ጌዜ ተብሎ የተቀመጠ ሲሆን በዚሁ መሰረት ተሰርቷል። /90%/ | | |
| | 2.11. የኣካዳሚክ ምክትል ፕረዚዳንት፤ የኮሌጅ ዲኖች ፤ ረጂስትራርና የተማሪዎች ዲን በየሁለት ሳምንት ኣንድ ጊዜ በመደበኛነት እየተገናኙ ክትትሎችና ምክክሮች ማካሄድ | የአካዳሚክ ምክትል ፕረዚዳንት ከኮሌጅ ዲኖች እንዲሁም ከረጂስትራርና ተማሪዎች ዲን ጋር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የትምህርት ክፍለ ሃላፊዎች ጋር በመገናኘት የአፈፃፀም እና የክትትል ስራዎችን ይሰራሉ /90%/ | | |
| | 2.12. የድጋፍ ሰጪ ምክትል ፕረዚደንትና በስሩ የሚገኙ ሃላፊዎች /ዳይሬክተሮች/ በየሁለት ሳምንቱ እየተገናኙ ክትትሎችና ምክክሮች ማድረግ | የድጋፍ ሰጪ ምክትል ፕረዚደንት ከተመደቡበት ጊዜ ጀምሮ ከሚመለከታቸው ሃላፊዎች ጋር እየተገናኙ በመስራት ላይ ናቸው /90%/ | | |
| | 2.13. የኮሌጅና የትምህርት ክፍል /ሁሉም የትምህርት ክፍሉ መምህራን የሚገኙበት/ ካውንስሎች በየሁለት ሳምንቱ ኣንድ ጊዜ በመደበኛነት እየተገናኙ ክትትል ማድረግና ውሳኔዎችን ማሳለፍ | የትምህርት ክፍል ካውንስሎች በየጊዜው እየተገናኙ ስራዎችን በመስራትና በመገምገም ላይ ይገኛሉ /100%/ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ግብ 3. የመምህራን ልማት ማጠናከር | 3.1 የመምህራን ልማት ፕላን የማውጣት አስፈላጊነት ታውቆ አስፈላጊ ዝግጅት ማድረግና ለፕላኑ መነሻ የሚሆኑ ነገሮችን ማዘጋጀት | ይህ እቅድ ከሶስተኛው ሩብ አመት ጀምሮ እንዲሰራ የተያዘ ሲሆን በተለይ በሚቀጥለው አመት ለምንቀበላቸው በርካታ ተማሪዎች እና ለምንከፍታቸው ሁለት አዳዲስ ኮሌጆች የሚያስፈልጉን መምህራን መሰረት በማድረግ ተጨማሪ መምህራን የሚገኙበት ስራ በመሰራት ላይ ነው። በ2005 የመምህራን ልማት ፕላነ በየደረጃው የሚዘጋጅ ይሆናል። | | |
| ግብ 4. ብቁ የአካዳሚክ ፕሮግራሞችና ስርኣተ ትምህርቶች ማረጋገጥና መተግበር፤ | 4.1 በተቀመጠው ዝርዝር መሰረት ኮሌጆችና የትምህርት ክፍሎችን ማደራጀትና ካሪከለሞችን በመሰብሰብና ማስተካከል የሚያስፈልጋቸው ካሉ በማስተካከል ተዘጋጅተው በየደረጃው ውይይት ተደርጎባቸው እንዲፀድቁ ማድረግ | ኮሌጆችና የትምህርተ ክፍሎች እንዲደራጁ ተደርጓል። መምህራን ወደ ተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ማቴርያሎችንና ካሪከለሞችን ስላመጡ በየትምህርት ክፍሉ ካሪከለሞቹ ተዘጋጅተው ውይይት ተደርጎባቸዋል። በኮሌጅ ደረጃ ፀድቀው በሰኔት የማፅደቅ ስራ ግን በ2004 ክረምት የሚከናወን ይሆናል። /አፈፃፀሙ 75 ፐርሰንት ነው/ | | |
| | 4.2 ተከታታይ ምዘና /Continuous Assessment/ እና መስፈርት ወይም ክራይተርያ መሰረት ያደረገ /Criterion Referenced/ የነጥብ ኣሰጣጥ ስርኣት መከተል። ለኣፈፃፀምም ይረዳ ዘንድ ኣስፈላጊ የኣፈፃፀም መመርያዎችን ማዘጋጀት፤ መግባባት መድረስ፤ ማስፈፀምና ኣፈፃፀሙን መከታተል | በእቅዱ መሰረት ስለ ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ እና ስለ አመዛዘን ሁኔታ ስልጠና ተሰጥቶ በየትምህርት ክፍሉ ውይይት ተደርጎበታል። ከዚሁም በተጨማሪ ህዳር 16 በተደረገው ጠቅላላ የመምህራን ስብሰባ ስለ ተከታታይ ምዘና እና የነጥብ አሰጣጥ ስርአት ተነስተው ውይይት ተደርጎባቸዋል። ተከታታይ ምዘና አስገላጊነቱ ላይ ስምምነት ተደርጎበት ከአንደኛ ሰሚስተር ጀምሮ ተግባራዊ ተደርጓል። የነጥብ አሰጣጥ በተመለከተ ግን መስፈርት መሰረት ያደረገው ስርአት የበለጠ መሆኑ ስምምነት የተደረሰበት ቢሆንም በአመቱ የተቀበልናቸው ተማሪዎች የመግቢያ ነጥባቸው ዝቅተኛ ስለሆነ ቋሚ መስፈርት ከተጠቀምን ተማሪዎቹ ሊጉዱ ይችላሉ የሚል ጉዳይ ተነስቶ እንደገና በየትምህርት ክፍሉ ውይይት እንዲደረግበት ከተደረገ በኋላ በሰኔት ደረጃም ውይይት ተደርጎበት ለአንደኛ ሰሚስተር ብቻ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው በማወዳደር የሚደረገው የነጥብ አሰጣጥ ተግባራዊ እንድናደርግ ከሁለተኛ ሰሚስተር ጀምሮ ግን ቋሚ መስፈርት የተከተለ የነጥብ አሰጣጥ ስርአት መከተል እንደሚገባ ውሳኔ ተሰጥቶበታል። | | |
| | 4.3 የደከሙ ተማሪዎችን በመለየት በተለይም ደግሞ የሴተ ተማሪዎችን መሰረት ያደረጉ የቱቶርያልና ረሜድያል ስራዎችን ማከናወን | ከተመደቡልን ተማሪዎች ወስጥ 65 ከመቶ የሚሆኑት ሴቶች ተማሪዎች መሆናቸው ለማወቅ ችለናል። የድጋፍ አሰጣጥ ስርአታችን በዚሁ መሰረት መቃኘን እንዳለበትም ተሰምሮበታል። ከሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው አካላት ምክክር ተደርጎበታል። | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | የትምህርት ክፍሎች ቱቶርያል ትምህርቶችን ሰጥተዋል። በአንደኛ ሰሚስተር በሁሉም ትምህርት ክፍሎች የቱቶርያል ድጋፎች ተሰጥተዋል።የአንደኛ ሰሚስተር ፈተና ተሰጥቶ በፈተናው ከተቀመጡት 844 ተማሪዎች ውስጥ ውጤት ከታየ በኋላ በድምሩ 103 ተማሪዎች (ከነዚህ ውስጥ 76 ሴት ተማሪዎች ናቸው) ከ1.5 በታች ውጤት በማግኘታቸው ውጤታቸው ከ1 ነጥብ በታች የሆኑት 25 ተማሪዎች /ከነዚህ ውስጥ 20 ሴት ተማሪዎች ናቸው/ ወይም በፐርሰንት ሲገለፅ ፈተና ከተቀመጡት ውስጥ 3 ከመቶ የሚሆኑት ዲስሚሳል እንዲሆኑ በሴኔት የተወሰነ ሲሆን ነጥባቸው አንድ እና ከዛ በላይ የሆኑ እና ከሁለት በታች ነጥብ ያገኙት ግን የድህረ ማጠናከርያ (Post Remedial) ትምህርት (ለአራት ሰአታት ተሰጥቶዋቸው) ለሁለተኛ ፈተና እንዲቀርቡ ስርአት ተበጅቶለት የተተገበረ ሲሆን በዚሁም መሰረት በርካታ ተማሪዎች ውጤታቸውን አሻሽለዋል። ሆኖም 18 ተማሪዎች እንደተፈለገው ውጤታቸውን ያላሻሻሉ ቢሆንም ኮርስ ቀንሰው የሁለተኛ ሰሚስተር ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ተደርጓል /አፈፃፀሙ 90 ፐርሰንት/ | | |
| | 4.4 በከተማው ከሚገኘው ሆስፒታል ጋር በመነጋገር የህክምና ኮሌጅ በማጠናከር ተማሪዎችን ማስተናገድና የጋራ ቅጥር በተመለከተ ስምምነት መድረስና ማስፈፀም | ከከተማው ሆስፒታል ጋር ንግግር ተደርጎ የመርህ መስማማት ተደርሶበታል። የጤና ሳይንስ ኮሌጅ በ2005 የትምህርተ ዘመን ለመጀመር ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል። ለዚህም ይረዳ ዘንድ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሶስት የሜዲካል ዶክተሮች እንዲመደቡልን በደብዳቤ ጠይቀን የነበረ ሲሆን ከክልሉ እንደሚመደቡልን ስምምነት ተደርሶ የነበረ በመሆኑ ምክንያት በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን። የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ለመጀመር ከከታማው ሆስፒታል ሃላፊዎችና ከዓይደር ሆስፒታለ ዲን ጋር በተደጋጋሚ ምክክሮች እየተደረጉ ነው። /85%/ | | |
| | 4.5 በኢንጂነሪንግ መስክ የEuropean Credit Transfer System ተግባራዊ ማድረግ | በሚመለከታቸው ትምህርት ክፍሎች ECTS መተግበር እንዳለበት ስምምነት በመደረሱ ህዳር 11/2004 አተገባበሩን በማስመልከት ስልጠና ለመምህራን ተሰጥቷል። በዚሁም መሰረት የፕሪኢንጂነሪንግ ተማሪዎች በኢሲቲኤስ ስርአት መሰረት በመማር ላይ ይገኛሉ። /አፈፃፀሙ 100 ፐርሰንት ነው/ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ግብ 5. የ70 በ 30 ቀመር ላይ የተመሰረተ ሃገራዊ የተሳትፎ መጠንን እውን ማድረግ፤ | 5.1 የተማሪዎች ስብጥር ወደዩኒቨርሲቲው በየባንዱ የሚመደቡ ተማሪዎች ብዛት የሚወሰን ቢሆንም ኣመዳደቡ 70 በ 30 ቀመር ላይ መሰረት ያደረገ እንደሚሆን ስለሚጠበቅ ይሄንን መሰረት ያደረገ የመምህራን ቅጥር ለማስፈፀም ጥረት ማድረግ | ከተመደቡልን 960 ተማሪዎች ውስጥ 69.5 በኢንጂነሪንግና በተፈጥሮ ሳይንስ ሲሆኑ ቀሪዎቹ 30.5 ደግሞ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስና በማህበራዊ ሳይንስ ናቸው። አሁን ትምህርት ላይ ያሉት 898 ተማሪዎች ደግሞ 69.93 በተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፍ ያሉ ሲሆን ቀሪዎቹ 30.07 ደግሞ በማህበራዊ ዘርፍ ያሉ ናቸው። ከነዚህ ተማሪዎች ደግሞ 42.3 በኢንጂነሪንግ መስክ የተመደቡ ናቸው። ስለዚህ የ70 - 30 ስብጥሩ ከወዲሁ ተግባራዊ መደረግ ጀምረናል። የሁለተኛ ሰሚስተር ትምህርተ እየተጀመረ ስለሆነ ስብጥሩ እንደገና ይሰላል /አፈፃፀሙ 100 ፐርሰንት ነው/ | | |
| ግብ 6. የከፍተኛ ትምህርት ፍትሃዊነት ማረጋገጥ፤ የተማሪዎች ተሳትፎ ማረጋገጥ | 6.1. የሴት ተማሪዎች እና ኣካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በተቻለ መጠን ቅድሚያ በመስጠት በመረጡዋቸው የትምህርት መስኮች እንዲመደቡ ማድረግ፤ | ለሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ቅድሚያ በመስጠት የትምህርት ክፍል ምደባ ተሰርቷል። ስፍራነሽ ነጋሽ የምትባል ከሸኖ አከባቢ ለመጣች ተማሪ እርጉዝ ስለነበረች ለወሊድ ወደ አከባቢዋ መሄድ ስለፈለገች ከዩኒቨርሲቲው ህብረተሰብ 2156 እና ከከተማው ሴቶች ማህበር 614 ብር በድምሩ 2700 ብር ተስጥቷት ተሸኝታለች። ሁለት ችግረኛ ተማሪዎች ደግሞ /መቅደስ ግርማ እና አረጌ አለምዋ/ ብርድ ልብስ፤ አንሶላ፤ የትራስ ለብስ እና ለአለምዋ ሳሙና፤ ደብተር፤ ሞዴስ ተገዝቶ ተበርክቶላቸዋል። ዊንታና ለምትባር አካል ጉዳተኛ ተማሪ ደግሞ ላጋጠማት የስብራት ችግር መታከምያ የሚሆን በድምሩ ከ10ሹ በላይ ብር ከዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ተዋጥቶላታል። ከዚሁ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ የሚይዘው ተማሪዎች የአንድ ጊዜ ምግባቸውን ከምንቸት ወደ ሽሮ ለመለወጥ ወስነው ከዚሁ የተገኘው ገንዘብ ነው። ከዚሁም በተጨማሪ የኢኮኖሚ ችግር ላለባቸው ሴት ተማሪዎች መደረግ ስላለበት የድጋፍ ማእቀፍ ከሴቶች፤ ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር በተላከልን የአፈፃፀም ማእቀፍ መሰረት 55 ሴት ተማሪዎችና 11 ወንድ ተማሪዎች የኢኮኖሚ ድጋፍ እንዲደረግላቸው በመልማይ ኮሚቴ ተመልምለው ድጋፉ እየተደረገላቸው ይገኛል። /አፈፃፀሙ 100 ፐርሰንት ነው/ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 6.2. የሴት ተማሪዎችን፤ ኣካል ጉዳተኞችን እና ከኣዳጊ ክልሎች የመጡ ተማሪዎችን ያማከለ የቱቶርያል እና የማጠናከርያ /ሬሜድያል/ ድጋፍ ማድረግ፤ የሴት ተማሪዎች በራሳቸው ፍጥነት እንዲማሩ የሚያስችለውን ኣካሄድ መከተል | አብዛኛዎቹ ተማሪዎቻችን ሴት ተማሪዎች በመሆናቸው ለሁሉም ተማሪዎች የቱቶርያል ድጋፍ ተሰጥቷል። ያም ሆኖ ግን ቀደም ብሎ እንደተቀመጠው የአንደኛ ሰሚስተር ውጤታቸው ሲታይ በርከት ያሉ ተማሪዎች ጥሩ ውጤት ስላላመጡ ከሁለት በታች እና አንድ እና ከአንድ በላይ ነጥብ ያላቸው ተማሪዎች እንዲጠቀሙበት የድህረ ሬሜድያል ስርአት ተፈፅሞ ከ70 በላይ ተማሪዎች ውጤታቸውን አሻሽለዋል። | | |
| | 6.3. የተማሪዎች ካውንስል እንዲመሰረት ድጋፍ ማድረግ፤ የተማሪ ክበቦች እንዲመሰረቱ ድጋፍ ማድረግ | ከየክፍሉ ሁለት ተማሪዎች የክፍል ተወካዮች ሆነው የተመረጡ ሲሆን በድምሩ 42 ተማሪዎች የክፍል ተወካዮች ሆነው ተመርጠዋል። እነዚህ ተወካዮች የተማሪ ካውንስል ምክር ቤት አባላት የሆኑ ሲሆን የካንውንስሉ ሰባት የስራ አስፈፃሚ አባላት ተወካዮቹ መርጠዋል። የተማሪዎች ካውንስል ተወካዮች በተለያዩ የዩኒቨርሲቲው እርከኖች በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ። ሁለት የተማሪ ክበቦች /የቻሪቲ ክለብ እና የአረንጓዴ ክበብ/ ተቋቁመው እንቅስቃሴ አድርገዋል። | | |
| | 6.4. የካውንስል /የተማሪ ተወካዩች/ በሰኔት፤ በኮሌጅ ካውንስል፤ በትምህርት ክፍል ካውንስል፤ በምግብና እንዲሳተፉ ማድረግ | የየክፍል ተወካዮች ከትምህርተ ክፍል ሃላፊዎች ጋር በተደጋጋሚ እየተገናኙ ስራዎችን በመከታተል ላይ እንደሚገኙ ከየትምህርት ክፍሉ ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል። የተማሮዎች ካውንስል አባላት በተማሪዎች ምግብ እና በአጠቃላይ አስተዳደራዊ ስራዎች በሰፊው በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ። | | |
| | 6.5. የተማሪ የክፍል ተወካዩች ማስመረጥ ከትምህርት ክፍል ሃላፊ ጋር ተከታታይ ግንኙነቶችን መፍጠር፤ በሰሚስተር ኣንድ ጊዜ በኮሌጅ ደረጃ ከክፍል ተወካዮች ጋር ግምገማ ማድረግ | ስራ በጀመሩ ትምህርት ክፍሎች ያሉን የሴክሺኖች ብዛት 21 ነው። በዚሁም መሰረት 42 የክፍል ተወካዮች ተመርጠዋል። ከተመረጡት ውስጥ 19 ወንዶች ሲሆኑ 23 ደግሞ ሴቶች ናቸው። የክፍል ተወካዮቹ በየጊዜው ከትምህርት ክፍል ሃላፊዎች ጋር እየተገናኙ ስራዎችን ይከታተላሉ። | | |
| ግብ 7. ለኢንዱስትሪ ልማት ኣስተዋፅኦ የሚያደርግ ተቋሚዊ ኣቅምን ማረጋገጥ፤ | 7.1 በኣከባቢው እና በክልሉ ከሚገኙ መካከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ትስስር ለመፍጠር የመነሻ ጥናቶችን ማድረግና መጀመር | ይሄንን በተመለከተ የተሰራው ዋና ስራ በኤፈርት ዋናው ፅ/ቤት አነሳሽነት በትግራይ የሚገኙ ሶስቱ ዩኒቨርሲቲዎች እና የኤፈርት /ትእምት/ ሃላፊዎች በተገኙበት ከትእምት ኩባንያዎች ጋር መኖር ስለሚገባው ውይይት ተደርጎበታል። በዚሁም መሰረት የመነሻ ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ውይይት እየተደረገበት ሲሆን የስምምነት ውል /Memorandum of Understanding/ ለመፈረም | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ምክክሮች እየተደረጉ ነው። | | |
| | 7.2 ጥቃቅንና ኣነስተኛ ድርጅቶችን ለመደገፍና ለማጠናከር ዝግጅቶችን ማድረግ | ከሚመለከተው የከተማው አስተዳደር ጋር በመነጋገር በተለይ የፅዳት ስራዎችን በዋናነት እንዲሁም የጥበቃ ስራዎችን ወደ ውጭ ለማውጣት እንደምንፈልግ እንዲያውቁት አድርገናል። በተጨማሪም የስጋ አቅርቦት ከማህበራት እንዲሆን ፈልገን የሚመለከታቸውን ያነጋገርን ቢሆንም አጥጋቢ ውጤት ስላላገኘንበት ለሚቀጥለው የትምህርት ዘመን ልናደርገው እንደምንችልና ከወዲሁ መዘጋጀት እንዳለባቸው ተግባብተናል። የሽሮ እና የበርበሬ አቅርቦትም እንዲሁ ከማህበራት እንዲሆን በሚቀጥለው የትምህርት ዘመን እንድናየው ውይይቶችን አካሂደናል። አንዳንድ ማህበራትና ግለሰቦች በግቢው ውስጥ አገልግሎቶችን ለመስጠት ጥያቄዎችን ያቀረቡልን በጨረታ መልክ እንዲወዳደሩ ተደርገው በተለይ ማህበራትና ስራ አጥ ወጣቶችን ያማከለ መስፈርት በማዘጋጀት አሸናፊዎች ተለይተው ውል ለማሰር በዝግጅት ላይ ናቸው። | | |
| | 7.3 የማህበረሰብ ኣገልግሎች ስራዎችን መለየትና በተወሰኑት ላይ የተቻሉትን ድጋፎች ማድረግ | በከተማው በድምቀት በተከበረው የመስቀል በአል ላይ ዩኒቨርሲቲው የራሱን ዝግጅት አድርጓል። በዩኒቨርሲቲ አከባቢ ከሚገኘው ህብረተሰብ ጋር በመነጋገር የውሃ አቅርቦች ችግር መኖሩን ለማወቅ ስለተቻለ በአከባቢው ሁለት ስራ ያቆሙ የውሃ ጉድጓዶች ስለነበሩ አንደኛው ያለወጪ ተሰርቶ ስራ እንዲጀምር ያደረግን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከሶስት ሺ ብር በላይ ወጪ በማድረግ ስራ ስለጀመረ ለማህበረሰቡ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። | | |
| ግብ 8. ሃገራዊ ፖሊሲንና ፋይዳን ያማከለ ተቿሚዊ የጥናትና ምርምር ኣቅምን መገንባት፤ | 8.1. ለምርምር ስራዎች ኣመቺ የሆነ ኣደረጃጀት መፍጠር | በዚህ አመት በዋናነት ዘግጅቶችን ለማድረግ እቅድ የተያዘ ቢሆንም በተለይ የክልሉ የትምህርት ቢሮ፤ ሶስቱ ዩኒቨርሲቲዎች እና ሌሎች ኮሌጆች የተሳተፉበት የትምህርት ጥራት ፎረም የተመሰረተ ስለሆን የትምህርት ጥራትን በተመለከተ የምርምር እና ድጋፍ ስራዎችን ከ2004 ጀምሮ መስራት እንዳለብን በደረስነው ስምምነት መሰረት ለዚሁ የሚሆን ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ከባጀታችን ሁለት መቶ ሺ ብር መድበን እንቅስቃሴ ጀምረናል። ከዚሁም በተጨማሪ መምህራን የጥናት ፕሮፖዛሎችን እንዲያቀርቡ ጥሪ ተደርጎላቸው 20 ፕሮፖዛሎች ቀርበው ከነዚህ ፕሮፖዛሎች ውስጥ በኮሚቴ የተመረጡት የተሻሉት ፕሮፖዛሎች ብር 323165.08 ባጀት ተመድቦላቸው በሙሉ ያልተጠናቀቁ ቢሆንም በአመቱ መሰራት ያለባቸወ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ስራዎች ተሰርተዋል። | | |
| | 8.2. የምርምር የትኩረት መስኮች /Research Thematic Areas/ ለመለየት በትምህርት ክፍሎችና ኮሌጆች የመጀመርያ ስራዎችን መስራት | የቴማቲክ ኤርያዎችን የመለየት ስራ ጅመሮች የተሰሩ ሲሆን በሚቀጥለው አመት ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል። | | |
| ግብ 9. የዩኒቨርሲቲውን ገቢ ምንጮች በብዛትና በመጠን ማጠንከር። | 9.1. የገቢ ምንጮች ሊሆኑ የሚችሉ መስኮችን መለየትና ዝግጅቶችንና እንቅስቃሴዎችን ማድረግ /ለምሳሌ የማታና የክረምት ትምህርቶች፤ የዎርክሾፕ ስራዎች፤ የማማከር ስራዎች፤ የምርምርና የትብብር ፕሮጀክቶችን መቅረፅ፤እንደስጋና ሌሎች የእንስሳት ውጤቶች የሆኑት የተማሪ ምግቦች በራስ ማቅረብ/ | የገቢ ምንጮችን የማዳበር ስራዎች በተመለከተ በሶስተኛው ሩብ አመት የተሰራው የማታ ትምህርት የመጀመር ስራ ነው። በዚሁም መሰረት የዳሰሳ ጥናቶች ከተደረጉ በኋላ መማር ለሚፈልጉ ጥሪ ተላልፎ ምዝገባ ተደርጎ በሶስት የትምህርት አይነቶች ትምህርት ለመጀመር በዝግጅት ላይ ነን። በዚሁም መሰረት በማኔጅመንት 60 ተማሪዎች /ከነዚህ አምስቱ በነፃ የሚማሩ የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች ናቸው/፤ በኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ 41 ተማሪዎች፤ እና በሲቪል ምህንድስና 111 ተማሪዎች /በምህንድስና ከተመዘገቡት ውሰጥ 7 የነፃ ትምህርት አድል የተሰጣቸው የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች ናቸው/ ተመዝግበው ትምህርት ይጀመራል። የማታ ተማሪዎች አሰራር ለመምራት የሚያስችል የውስጥ መመርያ ተዘጋጅቶ በሰኔት ውይይት ተደርጎበት የፀደቀ ሲሆን የዩኒቨርሲቲው ቦርድም አፅድቆት ስራ ላይ ውሏል። | | |

## 4. ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮችና የተወሰዱ/ሊወሰዱ የታቀዱ መፍትሄዎች

በ2004 የባጀት/የትምህርት ዘመን የስራ አፈፃፀም ላይ ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

### 1. የትራንስፎርመር ችግር፤

በወጣው ዲዛይን መሰረት በዩኒቨርሲቲው ግቢ መተከል ያለባቸው ሶስት ትራንስፎርመሮች ናቸው። ሆኖም አንድ ቀደም ብሎ ለግንባታ ስራ የተገጠመ ትራንስፎርመር እና ትምህርት ከመጀመራችን ጥቂት ቀናት በፊት የተገጠመው ሁለተኛ ትራንስፎርመር በግቢው ውስጥ ይገኛሉ። እነዚህ ሁለቱም በጊዚያዊነት የተገመጡ ናቸው እንጂ በዲዛይኑ መሰረት የተተከሉ ትራስፎርመሮች አይደሉም። ቀደም ብሎ የተተከለው ወደ አብዛኛው የግቢው ክፍል ኤሌክትሪክ የሚያሰራጭ ሆኖ ስርጭቱን የሚያደርገው ደግሞ በጊዚያዊነት በተተከሉት የስርጭት መስመሮች ነው። ሁለተኛው ትራንስፎርመር ደግሞ ለኪችን አከባቢ ኤሌክትሪክ የሚያሰራጭ ነው። ሁለተኛው ትራንስፎርመር መጀመርያ ሲገጠም ሶስተኛው ፌዝ ሊሰራ ባለመቻሉ በሁለት ፌዝ ብቻ አገልግሎት ሲሰጥ የነበረ ቢሆንም ኋላ ላይ ሶስት ፌዝ ሃይል በሚሰጥ ሌላ ትራንስፎርመር ተቀይሯል።

ተማሪዎችን ህዳር መጨረሻ ላይ እንደተቀበልን ከኤሌክትሪክ ሃይል ጋር ተያይዞ አጋጥሞን የነበረው ችግር በሃይል ማነስ ምክንያት በርከት ያሉ የተማሪዎች ዶርሚተሪዎች መብራት ያልነበራቸው መሆኑ ነበር። በዚሁም ምክንያት ብዙ ተማሪዎች በጨለማ ክፍል ለብዙ ቀናት እንዲኖሩ ተገደዋል። የተሰሩት ክፍሎች ተማሪዎች ከመግባታቸው ሁለትና ሶስት ቀናት በፊት ነበረ ሙከራ የተደረገላቸው። በዚህም ምክንያት ችግሮችን ለማስተካከል ጊዜ ስላልነበረ የህንፃ ርክክብ ሳይደረግ ነበር ተማሪዎች እንዲገቡ የተደረገው። ለማንኛውም የመብራት ችግር ለመፍታት የተሰወዱት መፍትሄዎች በሁለት ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ። የኤሌክትሪክ ባለሞያዎች በሀይል እጥረት ምክንያት ነው በርከት ያሉ የተማሪዎች መኝታ ክፍሎች መብራት ሊኖራቸው ያልቻለው ብለው ባቀረቡልን ፕሮፖዛል መሰረት ኪችን አከባቢ ብቻ እንዲያገለግል ከተገጠመው ትራንስፎርመር ብዙ ገንዘብ በማውጣት የኤሌክትሪክ ገመድ ገዝተን መስመር ከመሬት ስር በመዘርጋት ሁለት የዶርሚተሪ ብሎኮች ሃይል ከዛው እንዲያገኙ አድርገናል። ይህ መፍትሄ የተወሰነ ለውጥ ቢያመጣም ችግሩን በሙሉ ሊፈታው አልቻለም። ጉዳዩን በተመለከተ ከከተማው መብራት ሃይል ሰራተኞች ጋር ባደረግነው ምክክር በየክፍሉ የተገጠሙት ፍሎረሰንት መብራቶች በጣም ብዙ ሃይል ስለሚያስፈልጋቸው መብራቶቹን ሃይል ቆጣቢ በሆኑ መብራቶች እንድንተካቸው በሰጡን ምክር መሰረት መብራት ባልነበረባቸው ክፍሎች የሚገኙትን ፍሎረሰንት አምፑሎች በሃይል ቆጣቢ አምፑሎች በመቀየር ችግሩ ሊፈታ ችሏል።

በ2005 የትምህርት ዘመን በርከት ያሉ ተጨማሪ ተማሪዎችን ለመቀበል የሚያስችሉን የመጀመርያው ዙር ሶስት አራተኛ ክፉይ 36 ብሎኮች እያለቁ መሆናቸው ቀደም ብሎ የተቀመጠ ሲሆን እነዚህን ልንጠቀምባቸው የምንችለው ግን የኤሌክትሪክ አገልግሎት ከተገጠመላቸው ነው። አሁን ያለው የሃይል አቅርቦች በቂ አይደለም ብቻ ሳይሆን በጊዚያዊነት የተገጠመ ስለሆነ በመዘርጋት ላይ ካለው የውስጥ ለውስጥ የኤሌክትሪክ መስመር ጋር የማይስማማ ነው። ስለዚህ በዲዛይኑ ውስጥ የተቀመጡት ሶስት ትራንስፎርመሮች ካልተገጠሙ ተጨማሪ ተማሪዎችን ለመቀበል አያስችለንም። ከዚህ እውነታ ጋር በመነሳት ለሶስት ትራንስፎርመሮች መትከያ የሚሆን ገንዘብ በዓዲግራት ቤቶች ልማት በኩል ክፍያ ስለተፈፀመ

በክረምር ወራት ትራንስፎርመሮቹ ተገጥመው ለ2005 ተማሪ ቅበላ ይደርሱልናል ብለን እየጠበቅን ነው። የመስመር ዝርጋታው በመሰረተ ልማት ኮንትራክተሩ በኩል እየተጠናቀቀ በመሆኑ አሁን በጥቅም ላይ ወደዋሉት ህንፃዎች /አንድ አራተኛ/ እና በቅርቡ ለሚጠናቀቁት ህንፃዎች /ሶስት አራተኛ/ መስመሮች ተዘርግተው ለ2005 የትምህርተ ዘመን መድረስ ይኖርባቸዋል።

## 2. በተማሪዎች ዶርሚተሪዎች ውስጥ የሚገኙት ሽንት ቤቶችና የፍሳሽ አገልግሎቶች ችግሮች ያሉባቸው መሆን፤

ከላይ እንደተገለፀው ተማሪዎቹ ወደ መኝታ ክፍሎች እንዲገቡ የተደረገው መደበኛ የህንፃ ርክክብ ሳይደረግ ነበር። የፍሳሽ ሙከራው የተጀመረውም ተማሪዎቹ ከመግባታቸው በፊት ባሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ ነው የነበረው። የመኝታ ክፍል ፍሳሽ ማስወገጃዎችን በተመለከተ ያጋጠመው ችግር በሁለት መልክ የሚታይ ነው። አንደኛውና ዋነኛው የአሰራር ችግር የነበራቸው በመሆኑ ተማሪዎች መጠቀም ሲጀምሩ የመዘጋት፤ ተገባጠሚዎች አከባቢ የመላቀቅና የማፍሰስ፤ እና ሌሎች ችግሮች የነበሩባቸው በርካታ ሽንት እና ሻወር ቤቶች አጋጥመዋል። ሁለተኛው ችግር ደግሞ ተማሪዎች እንደመጡ የአጠቃቀም ችግር /ለምሳሌ በሽንት ቤት መስመሮች ላይ ጨርቆችን ማስገባት/ ታይተዋል። ለተማሪዎች በፕሮክተሮች በኩል የሽንት ቤት አጠቃጠም ገለፃ ከተደረገላቸው በኋላ እና የፍሎር ተወካዮች ተመርጠው እንዲሰሩ ከተደረገ በኋላ የአጠቃጠም ችግሩ በዋናነት ሊቀንስ ችሏል። ከፍሎር ተወካዮች በተጨማሪ የየብሎክ ተወካዮች ተመርጠው ከፕሮክተሮች ጋር በመተባበር በመስራት ላይ ይገኛሉ። በሌላ በኩል ደግሞ በሽንት ቤቶች እና ፍሳሽ አገልግሎቶች የታየው ችግር ኮንትራክተሮች እንዲያስተካክሉ ተነግሮዋቸው ማስተካከያዎችን ለማድረግ ሙከራዎችን ያደረጉ ሲሆን ችግሮቹ አሁንም ሙሉ በሙሉ ሊፈቱ ያልቻሉ ናቸው። ችግሩ በዋናነት የአሰራር እና የሞያ ችግር ነው። ምናልባትም ችግሩ በቀላሉ የማይፈታ ስለሚመስል በቆርቆሮ ቤት ተለዋጭ ሽንት ቤቶችን የመስራት አማራጭ መታየት ይኖርበታል።

የተጠቀሰው ችግር በተመለከተ የግንባታው ኮንሳልታንት ከሆነው ገሬታ ኮንሳልታንት ጋር ተደጋጋሚ ውይይት አድርገንበታል። በዲዛይኑ መሰረት የመታጠብያ እና የሽንት ቤት መስመሮች ተለያይተው የሚወርዱ ስለሆነ ምናልባት ሁለቱም ተያይዘው አንድ ላይ እንዲወርዱ ቢደረግ ችግሩን በተወሰነ መልኩ ሊፈታው እንደሚችል መግባባት ላይ ስለደረስንበት በመገንባት ላይ ካለው የሶስት አራተኛው ክፋይ ጀምሮ አመቺ በሆኑት የተማሪዎች መኝታዎች /ትላልቆቹ የተማሪዎች መኝታዎች ማለትም Dormitory court yard type/ ላይ የመታጠብያና የሽንትቤት መስመሮች አብረው እንዲወርዱ በሌሎች መኝታ ቤቶች ላይ ደግሞ ከአንድ ወራጅ መስመር /ማለት ራይዘር/ ይልቅ በሁለት ወራጅ መስመሮች /ራይዘር/ እንዲስተካከሉ መግባባት ተደርሶ በዚሁ መሰረት እየተሰራ ይገኛል። በሁለተኛው ዙር ግንባታ ላይም ተመሳሳይ ወይም የተሻሉ መስተካከሎች እንዲደረጉ መግባባት ላይ ደርሰንበታል።

የመጀመርያ ዙር አንድ አራተኛው ክፋይ የመጀመርያ ርክክብ ያደረግን ሲሆን የመጨረሻው ርክክብ የሚደረገው እና የሪቴንሽን /Retention/ ክፍያ የሚለቀቀው ጥቅምት ወይም ህዳረ 2005 ስለሚሆን እስከዛው ድረስ በተለይ የተማሪዎች ሽንት ቤቶች አከባቢ ያሉት ጉድለቶች እንደገና እንዲሰሩ ኮንትራክተሮች እንዲፈርሙ ተደርጓል። ስለዚህ የመጨረሻ ርክክብ ከመደረጉ በፊት እንዚህ መስተካከሎች የሚደረጉ ይሆናሉ። በቅርቡ ከህንፃው ኮንሳልታንት /ገሬታ/ የተላከው ሳኒተሪ ኢንጂነር እንዳመለከተው ችግሮቹ የተፈጠሩት ተገቢ እቃዎች /ማለትም በ45$^{o}$ ቱቦ መሰራት የነበረባቸው በT ቱቦ መሰራታቸው እንዲሁም የSmell Trap

እቃዎች ጥራት የጎደላቸው መሆኑ/ ካለመጠቀምና ከአሰራር /workmanship/ ችግር እንዲሁም ከተማሪዎች አጠቃቀም ጉድለት መሆኑ ለመረዳት ተችሏል። በዚሁም መሰረት ውይይት ተደርጎበት የመጨረሻው ርክክብ ከመደረጉ በፊት እቃዎቹም አሰራሩም መስተካከል እንዳለባቸው የተስማማንበት ሲሆን በገሬታ በኩል ለኮንሳልታንቶቹ እንዲነገራቸውና እንዲያስተካክሉዋቸው የሚደረግ ይሆናል።

3. **ግቢው አጥር የሌለው መሆን፤**
ግቢው በአጥር ያልታጠረ ስለሆነ ለጥበቃና ለክትትል ቀላል ሊሆን አልቻለም። በዚህ ምክንያት እስካሁን ያጋጠመ ችግር ባይኖርም ችግሮች ማጋጠማቸው የማይቀር ነው። ቀደም ብሎ ግቢዎችን በአጥር የማጠር ጥያቄ ለትምህርት ሚኒስቴር አንስተንላቸው የነበረ ቢሆንም የሚጠይቀው ባጀት ከፍተኛ ስለሆነ ከኛ በፊት ስራ የጀመሩት ዩኒቨርሲቲዎችም መደበኛ አጥር ሊያደርጉ አልቻሉም። ስለዚህ መደበኛ አጥር የማድረጉ ጉዳይ ላይፈታ ስለሚችል በቀላል አጥርና በተስማሚ ተክሎች የማጠር አማራጭ መወሰድ ይኖርበታል ተብሎ አቅጣጫ መቀመጡ የሚታወስ ነው። በተለይ በተስማሚ ተክል /ማለትም ኮሽም/ የማጠር ስራ ድርብ ጠቀሜታ ያለው ስለሆነ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ የሚገባው ጉዳይ ነው። ለዚሁም ይረዳን ዘንድ መጀመርያ የዩኒቨርሲቲው ግቢዎች ድንበር በትክክል መመልከት ስለሚኖርበት ባለሞያዎችን በመቅጠር ድንበሩን በትክክል እንዲያመለክቱልን ውል ገብተን ምልከታው በዋናው ግቢ ተስርቶ አልቋል። የድንበር ምልከታው ከተደረገ በኋላ በጊዜያዊ አጥር /በባህርዛፍ ምሰሶዎችና በችርኳላታ ብረት/ እንዲታጠር ተደርጓል። ከዚሁም ጎን ለጎን የኮሽም እና ሌሎች ወበት ሰጪ /Ornamental/ ተክሎች በመተከል ላይ ይገኛሉ።

ከግቢው ምልከታ ጋር ተያይዞ ወደ ዛላንበሳ ከሚሄደው ዋና የአስፋልት መንገድ ወደ ዩኒቨርሲቲው የሚያገናኝ መንገድ /ከተቻለ የአስፋልት መንገድ የሚሆን/ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ከከተማው አስተዳደር ጋር ተደጋጋሚ መፃፃፍና ምክክር ተደርጎበት አሁን መስመሩ የተዘጋጀ ሲሆን ካሳ የሚከፈላቸው ተከፍሏቸው ጠረጋው በአጭር ጊዜ እንደሚጠናቀቅ ይጠበቃል። ዩኒቨርሲቲው ይህ መንገድ አስፋልት ሊሆን የሚችልበት አማራጭም ማፈላለግ ይኖርበታል።

4. **የላቦራቶሪዎች እና የዎርክሾፖች አለመሟላት፤**
አንድ የላቦራቶሪ ብሎክ የተጠናቀቀ ቢሆንም የላቦራቶሪ እቃዎች አልደረሱልንም። በተለይ በተፈጥሮ ሳይንስ መስክ የሚማሩ ተማሪዎች ደግሞ ካለ ላቦራቶሪ አገልግሎት ትምህርት መስጠቱ ትምህቱን ሙሉ አያደርገውም። ስለዚህ ሌሎች አማራጭ መፍትሄዎች መወስድ ይኖርባቸዋል። በዚሁም መሰረት በአንደኛ ሰሚስተርና በሁለተኛ ሰሚስተር ተማሪዎችን ወደ መቐለ ዩኒቨርሲቲ በመውሰድ የላቦራቶሪ ስራ እንዲሰሩ በማድረግ ችግሩን ለማቃለል ተችሏል። ከዚህም በተጨማሪ በራሳችን ግዥ ማማላት ያለብንን እቃዎች ለማማላት ጥረት እየተደረገ ነው። እንደጥሩ ምሳሌ ሊጠቀስ የሚችለው በሜካኒካል ምህንድስና የሚፈለጉና በገበያ የሚገኙ ቀላል ማቴርዩሎችን በግዥ እንዲቀርቡ ተደርገዋል።

ዎርክሾፖችን በተመለከተ ደግሞ በርከት ያሉ /በተለይመ የሜካኒካል ምህንድስና/ ማቴርያሎች ቀደም ብሎ በተገባው ውል መሰረት የደረሱን ቢኖንም የዎርክሾፕ ህንፃዎች ባለማለቃቸው ምክንያት ማሽነሪዎቹ ሊተከሉና ጥቅም ላይ ሊውሉ አልቻሉም። ህንፃዎቹ በመጠናቀቅ ላይ በመሆናቸው ተከላው እና የአጠቃቀም ስልጠናው /በአቅራቢዎች በኩል/ ተሰጥቶ የ2005 ትምህርት ከመጀመሩ በፉት ይደርሱልናል ብለን እየተጠባበቅን ነው። ይህ እስኪሆን ድረስ ግን የምህንድስና ተማሪዎች /በተለይ የሲቪል እና የሜካኒካል/ በሁለተኛ

ሰሚስተር የተግባር ስልጠናዎች መውሰድ ስለሚጠበቅባቸው በከተማው ከሚገኘው የፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ጋር ስምምነት በማድረግ ተማሪዎቻችንን እዛ ድረስ እየላክን የቤተሙከራ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛሉ። ችግሩን ለጊዜው በዚህ መልኩ መፍታት የተቻለ ቢሆንም ለ2005 ግን በራሳችን ላቦራቶሪዎችን ዎርክሾፖች ለመጠቀም የተጠናከሩ ዝግድቶች ያስፈልጋሉ።

5. **የመፃህፍት አቅርቦት ማነስ፤** የዩኒቨርሲቲው ቤተመፃህፍት እስከ ምሽቱ አራት ሰአት አገልግሎት መስጠት የጀመረ ቢሆንም የመፃህፍት አቅርቦቱ ግን ገና እዚህ ግባ የማይባል ነው። መፃህፍቶችንና የማስተማርያ ማቴርያሎችን ለማግኘት የተደረጉ ጥረቶች እንዳሉ ሆነው ገና ብዙ ይቀራል። ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር ባደረግነው ንግግር በርካታ መፃህፍት እንደሚላኩልን /በግዥ/ ተነግሮን የነበረ ቢሆንመ እስካሁን የደረሱን ግን የተወሰኑት /በዋናነት በምህንድስና/ ብቻ ናቸው።በራሳችን የማባዛት አቅም ተጠቅመን እና በራሳችን ግዥ ያገኘናቸው መፃህፍትም ጠቃሚ አስተዋፅኦ ያደረጉ ነበሩ። በተለይ መጠቀስ ያለበት ለምርምር ተመድቦ የነበረው ባጀት የተወሰነው ጥቅም ላይ ባለመዋሉ ምክንያት የብር 170000.00 መፃህፍት ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ጋር በመፃፃፍ በለቀማ ገዝተን ጥቅም ላይ አውለናል።

6. **የሲቪል ምህንድስና መምህራን እጥረት፤**

በምደባም፤ በቅጥርም፤ በዝውውርም የሲቪል ምህንድስና መምህራን ለማግኘት ጥረቶች የተደረጉ ቢሆንም እስካሁን በምደባ ያገኘናቸው ቀደም ብሎ ሁለት ቆይቶም ተጨማሪ ሁለት በድምሩ አራት መምህራን ብቻ ናቸው። ሆኖም በተለይ የኢንጂነሪንት ተማሪዎች ዋነኛው ምርጫቸው የሲቪል ምህንድስና ከመሆኑ አንፃር የመምህራኑ ቁጥር በጣም አንስተኛ ስለሆን ተጨማሪና ተከታታይ ጥረት ያስፈልጋል። ተጨማሪ የሲቪል ምህንድስና መምህራንን በቅጥርም በዝውውርም የማግኘቱ ጥረት የሚቀጥል ይሆናል።

7. **የሴፕቲክ ታንክ መሙላት እና መፍሰስ**

የፍሳሽ ማጠራቀምያ በተመለከተ እንደ ዘላቂ መፍትሄ የተቀመጠው የትሪትመንት ፕላንት ግንባታ ነው። ሆኖም እስካሁን የተሰራው የሴፕቲክ ታንክ ብቻ ሲሆን ሌላው ክፍል ግንባታ አልተጀመረም። የተገነባው ሴፕቲክ ታንክ ደግሞ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ከጥቂት ቀናት በኋላ ሞልቶ መፍሰስ (overflow) ጀምሮ በአከባቢው ላይ ብክለት እንዳያስከትል ስጋቶች አሉ። በመጣጭ መኪና ለመምጠጥ የተሞከረ ቢሆንም ይሂም ጥሩ ውጤት ያመጣ ስራ አይደለም። በተለይ የከተማው አስተዳደር የፍሳሽ መጣጭ መኪና በቅድሚያ እንድንጠቀምበት ፈቅደውልን የነበረ ቢሆንም ጥቂት አገልግሎት ከሰጠን በኋላ መበላሸቱ የመምጠጥ ስራውን አስቸጋሪ አድርጎታል። የትሪትመንት ፕላንት ግንባታም በቶሎ ሊደርስ እንደማይችል ግምት ውስጥ በማስገባት በሚቀጥለው አመት የራሳችን መጣጭ መኪና እንዲገዛልን በካፒታል ባጀት እንዲያዝልን ጥያቄ አቅርበን ተቀባይነት አግኝቷል። መኪናው እስኪመጣ ደግሞ የመሰረተ ልማት ስራዎችን ከሚያካሂደው ጋር በመነጋገር የትሪትመንት ፕላንቱ አካል የሆኑት ክፍሎች ቶሎ እንዲሰሩ የማድረጉ ጥረት ደግሞ የምንቀጥልበት ይሆናል። በሌላ በኩልም የተሰራው ኤፕቲክ ታንክ የተቀመጠበት ቦታ ተዳፋት የሆነና የጎርፍ መውረጃ በሆነ አከባቢ መሆኑ ለችግሩ መባባስ ተጨማሪ ምክንያት ሆኗል። ይህ የፍሳሽ ችግር በ2005ም በወሳኝነት የሚፈታ ችግር አይመስልም። ሆኖም ግን ከገሬታ ጋር ባደረግነው ውይይት ተጨማሪ ሴፕቲክ ታንክ ለመስታት ዲዛይኑን በነሱ በኩል ክትትሉን ደግሞ በኛ

በኩል እንድንሰራው ተስማምተናል። የደረቅ ፍሳሽ ማሰራቱ ጉዳይም ሌላው የመፍትሄ አካል ይሆናል።

## 8. ተጫራቾች ያሸነፉትን እቃ በወቅቱ አለማቅረብ እና ከዋጋ መናር ጋር ተያይዞ ያጋጠሙ እክሎች

በባጀት አመቱ ሌላው ያጋጠመው ችግር አሸናፊ ተወዳዳሪዎች ያሸነፉዋቸውን እቃዎች በወቅቱ ያለማቅረብና ከዋጋ ንረት ጋር ተያይዞ የዋጋ ይጨመርልን ጥያቄ በአቅራቢዎች መቅረቡ ነበር። በወቅቱ ያሸነፉዎዋቸውን እቃዎች ያለማቅረብ ጉዳይ በተለይ በባጀት አመቱ መጨረሻ አከባቢ ይቀርቡልናል ብለን የጠበቅናቸው የኮንፒዩተር አቅርቦት በያናነት የሚጠቀሰው ነው። ከዋጋ መጨመር ጋር ተያይዞም በዋናነት የሚጠቀሰው የጤፍ አቅርቦት ጉዳይ ነበር። የጤፉ ጉዳይ በተመለከተ ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ጋር ተፃፅፈን በሌላ ውድድር እንድንገዛ ተፈቅዶልን ችግሩ ሊፈታ ችሏል። ሆኖም በተለይ ከዋጋ መለዋወጥ ጋረ ተያይዞ ለሚፈጠረው ችግር እንደዘላቂ መፍትሄ በግዥ መመርያው እንደተቀመጠው የፍሬምወርክ ግዥ ማካሄድ ይሆናል። በዚሁም መሰረት ለ2005 የባጀት አመት በፍሬምወርቅ /ማእቀፍ/ ግዥ መገዛት ያላቸው እቃዎች በመለየት /ጤፍ፤ ስጋ፤ አትክልቶች፤ ወዘተ/ በዚሁ መሰረት እንዲገዙ ዝግጅቶች በመደረግ ላይ ናቸው።